ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት ፪

ከዚህም ፡ ሠራኢ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ትን መቂ ፡ ምን ፡ ምግባር ፡ ያሻል ፡ ብለዋል ፡
ሣኤ ፡ መታን ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይጸፉል ፡ ቀዳሚት ፡ ብሎ ፡
ር ፡ የለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ካመኑ ፡ ከተጠ ነበረና ፡ ዳግሚት ፡ አለ ፡ (ምክንያት) ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአንትሙኒ፡ በሰሉ፡ ጕጕኣ ፡ በል ፡ ፩፡ ፭። ወይእዜኒ፡ አኀዊነ፡ ጕጕኡ፡ በል ፡ ፩ ፡ ፲ ። ወዘንተ ፡እንዘ፡ ትገብሩ፡ በል፡ ም፡ ፩፡ ፲፩። ወበእንተ፡ ዝ ፡ እጽህቅ ፡ በል ፡ ም፡ ፩፡ ፲፪። ወይመስለኒሰ ፡ ከመ፡ ርቱዕ፡ በል፡ ፩፡ ፲፫። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኖኅን ፡ ከድምሳሴ ፡ ሎጥን ፡ ከግፍታኤ ፡ እንዳዳነ ፡ ይናገራል ፡ ወዕለቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በል፡ ፲ ፡፲ ። ሐዲሰተ ፡ ሰማያት ፡ ወሐዳሰ ፡ ምድረ ፡ ንሴፎ ፡ ይላል ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡ የጸፈበት ፡ ሀገር ፡ ግብፅ ፡ ክታብ ፡ ወሳጅ ፡ የለም ። አንድም ፡ አልሚናስ ፡ ጳውሎስ ፡ አልንጳስ ፡ ጳውሎስ ፡ (እምኅበ ፡ ስምዖን ፡ ኬፋንና ፡ ወዘንተ ፡ ባሕቱ ፡ ቅድሙ ፡ አእምሮን ፡ ምክንያት ፡ ያደርጋሉ) ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እምኅበ ፡ ስምዖን ፡ ኬፋ ።

ስምዖን ፡ ማለት ፡ ሰምዐኒ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት ፡ ነው ፡ ኬፋ ፡ ማለት ፡ መሠረት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ከሌለ ፡ እናት ፡ አባቴ ፡ ማን ፡ ስምቷቸው ፡ ሰምዐነ ፡ አሉ ፡ እኔስ ፡ የማነን ፡ ሃይማኖት ፡ መስክሬ ፡ መሠረት ፡ ተባልሁ ፡ ሲል ፡ እምኅበ ፡ ስምዖን ፡ ኬፋ ፡ አለ ። አንድም፡ ስምዖን ፡ በብሉይ ፡ የወጣለት ፡ ስም ፡ ነው ፤ ኬፋ ፡ በሐዲስ ፡ የወጣለት ፡ ስም ፡ ነው ፡ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ባለቤት ፡ እኔ ፡ ሳለሁ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ለምን ፡ ያፍልብኛል ፡ ሲል ፡ እምኅበ ፡ ስምዖን ፡ ኬፋ ፡ አለ ። አንድም ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ፡ ረዐይኬ ፡ መሐስዕየ ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕትየ ፡ ብሎ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ የሾመኝ ፡ እኔ ፡ ሳለሁ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ለምን ፡ ያፍልብኛል ፡ ሲል ፡ እምኅበ ፡ ስምዖን ፡ ኬፋ ፡ አለ ።

ገብሩ ፡

አገልጋዩ ፡ ከምሆን ፡ (ባለሚሉ) ።

ወልኡኩ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ከማስተምር ፡ ከኔ ፡ ከጴጥሮስ ፡ የመጣች ፡ ክታብ ፡ ለእለ ፡ ነገብር ፡ ክብረ ፡ በሃይማኖት ፡

በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ሆነን ፡ በልጅነት ፡ ለምንተባበር ፡ ትድረስ ፡

እንተ ፡ ከፈለን ፡ በጽድቁ ፡ ለአምላክነ ፡ ወፈራቂነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ለ ፡ ጽድቁን ፡ ሲያይ ፡ የገባ ፡ ነው ፤ (ጥቅ)፡ ወረሰየ ፡ ቀዳማየ ፡ መድኀኒቶሙ ፡ በኃይሉ ፡ ለቃል ፡ ዘኮነ ፡ ፭ደ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ እንዲል፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚያደላት ፡ በልጅነት ፡ ለምንተባበር ፡ ትድረስላቸው ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈጣሪያችን ፡ በመድኀኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካሣ ፡ ባደለን ፡ በልጅነት ፡ ለምንተባበር ፡ ትድረስ ፡

ሞገስ ፡ ወሰላም ፡ ይብዛኅ ፡ ለክሙ ።

ሞገስ ፡ ሰላም ፡ ይደረግላችሁ ፡ ትርጓሜ ፡ እንዳለፈው ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፪ ፤ በአእምሮቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡አግዚእነ ።

ፈጣሪያችን ፡ ወእግዚእነ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማወቅ ። አንድም ፡ ከማወቅ ፡ ጋራ ። አንድም ፡ በማወቅ ፡ ላይ ፡ ይደረግላችሁ ።

፫ ፤ ዘበኀይል ፡ መለኮቱ ፡ ወሀበ ፡ ለነ ፡ ኵሎ ፡ ምግባረ ፡

በመለኮታዊ ፡ ሥልጣኑ ፡ ዳያነ ፡ ፈውሱ ፡ ሙታነ ፡ አንሥኡ ፡ እለ ፡ ለምዕ ፡ አንጽሑ ፡ ኢጋንንተ ፡ አውዕኡ ፡ ብሎ ፡ ገቢረ ፡ ተአምራትን ፡ የሰጠን ፡

ዘይወስድ ፡ ኅበ ፡ ሕይወት ፡ ወጽድቅ ፡

(ሕይወት) ፡ ሙታንን ፡ ወደ ፡ ትንሣኤ፡ ድውያንን ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ (ጽድቅ) ፡ አሕዛብን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ኃጥአንን ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚያደርስ ፡

ውእቱ ፡ ዘጸውዐነ ፡ ውስተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወውስተ ፡ ሠናይቱ ።

ይኸውም ፡ እኛን ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ጌትነቱ ፡ ወደ ፡ በጐነቱ ፡ የጠራበት ፡ ነው ፡ አለ። (ስብሐቲሁ)፡ ከሃለ ነቱን፡(ሠናይቱ)፡ አምጸአ ፡ ዓለማትነቱን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ የጠራበት ፡ ነው ፡ (ጥቅ) ፡ ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ነአኵቶ ፡ ለገባሬ ፡ ሠናያት ፡ ላእሌነ ፡ እንዲል ። አንድም፡ስብሐቲሁ ፡ ፩ነቱን ፡ ፫ነቱን ፡ ሠናይቱ ፡ ሥጋዌውን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ የጠራበት ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ።

፬ ፤ በዘቦቱ ፡ ነሐዩ ፡

በሱ ፡ በማመን ፡ ጸንተን ፡ በምንኖር ፡ ገንዘብ ፡ (ጥቅ) ፡ ባቲ ፡ ነሐዩ ፡ ባቲ ፡ ንመውት ፡ ባቲ ፡ ንትቀበር ፡ ባቲ ፡ ንትነሣእ ፡ እንዲል ፡

ወነዐቢ ፡

እሱ ፡ ከሚሠራው ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ በምንሠራ ፡ ገንዘብ ፡

ወንክብር ፡

በምንከብር ፡ ገንዘብ ፡ (ጥቅ) ፡ ወከብረት ፡ ነፍሶሙ ፡ በውስተ ፡ ዓለማት ፡ ክልኤቲ ፡ ዘዝየ ፡ ወዘኩሓ ፡ እንዲል ፡ በወዲሁ ፡ አማልክት ፡ ተመሰሉ ፡ ሰብአ ፡ ወወረዱ ፡ ኀቤነ ፡ ይሏቸዋል ፡ በወዲያውም ፡ ወሀሎ ፡ ይትዌሰክ ፡ ሥን ፡ በዲበ ፡ ሥን ፡ እንዲል ፡ ተወስኮ ፡ ዘነሣእያን ፡ አያቋርጥምና ፡

በተስፋሁ ፡ እንተ ፡ ጸገወነ ፡

ነዐቢ ፡ ላለው ፡ እመ ፡ ቦ ፡ ዘየአምን ፡ ብየ ፡ ግብረ ፡ ዘአነ ፡ እገብር ፡ ይገብር ፡ ወዘየወቢ ፡ እምኔሁ ፡ ይገብር ፡ ብሎ ፡ በነገረነ ፡ ተስፋ ፡ ንከብር ፡ ላለው ፡ አንትሙ ፡ ትነብሩ ፡ ዲቤ ፡ ፲ወፎቱ ፡ መናብርት ፡ ብሎ ፡ በነገረነ ፡ ተስፋ ፡ በምንኩበር ፡ ገንዘብ ፡ ጽውዐነ ፡ ላለው ፡

ከመ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡

ማንሻ ፡ ነው ። አንድም ፡ በተስፋሁ ፡ እሙውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ብሎ ፡ ባናገረው ፡ ተስፋ ፡

ከመ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ትኩኑ ፡ ሱቱፋነ ፡ ለመለኮተ ፡ ዚአሁ ።

ጌትነቱን ፡ ለማገልገል ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ተባባሮች ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡

እንዘ ፡ ትጐይዋ ፡ ለፍትወተ ፡ ሙስናሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ።

ስለዚህ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ አጥፊ ፡ ፈቃዱን ፡ እየሸሻችሁ ፡ እየራቃችሁ ።

፭ ፤ ወእንትሙኒ ፡ በዙሉ ፡ ጕጕኣ ፡ ገቢረክሙ ፡

በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ችኮላን ፡ አድርጋችሁ ፡

አትልውዋ ፡ ለሠናይት ፡ በ፫ይማኖትክሙ ፡

በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ምግባርን ፡ የዙ ፡

ወበሠናይት ፡ ለአእምሮ ፡

በምግባርም ፡ ላይ ፡ ፈሊጥን ፡ ያዙ ። ገላት ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፳፪ ።

፮ ፤ ወበአእምሮ ፡ ለኢዘምዎ ፡

በፈሊጥም ፡ ላይ ፡ ንጽሕናን ፡ ያዙ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወበኢዘምዎ ፡ ለትዕግሥት ፡
በንጽሕናም ፡ ላይ ፡ ትእዕግትን ፡ ያዙ ፡
ወበትዕግሥት ፡ ለአምልኮ ፡
በትዕግሥትም ፡ ላይ ፡ ሁነኔ ፡ ወልደ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ ያዙ ።
፮ ፤ ወበአምልኮ ፡ ለተአኅዎ ፡
በሁነኔ ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔርም፡ ላይ ፡
ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ መበባልን ፡ ያዙ ።
ወበተአኅዎ ፡ ለተፋቅሮ ፡
ወንድሜ ፡ ወንድሜ፡ በመበባልም፡ ላይ ፡
ፍቅርን ፡ ያዙ ። ሐተታ ፡ የቃል ፡ ዘመደ ፡
በገባያም ፡ አይገድ ፡ እንዲሉ ፡ የነደለ
ውን ፡ በመምሳት ፡ የጠመመውን ፡ በማ
ቅናት ፡ ገላት ፡ ፮ ፡ ፲ ።
፰ ፤ ወዝንቱ ፡ ኩሉ ፡ እምኀመ ፡ ሀለወ ፡ ኀቤክሙ ፡
ኢኮንክሙ ፡ ፅሩዓነ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ካለ ፡ ሥራ ፡
ፈት ፡ አትባሉም ፡
ወኢኮንክሙ ፡ አለ ፡ እንበለ ፡ ፍሬ ።
ያለ ፡ ፍሬ ፡ ትሩፋትም ፡ አላችሁ ፡ አት
ባሉም ።
አላ ፡ ያበጽሐክሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮቱ ፡ ለእግዚአነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ያደ
ርሳችኋል ፡ እንጅ ፡ (እሱ ፡ የሠራውን ፡ ለ
መሥራት ፡ ያበቃናል ፡ ሲል ፡ ነው) ። አን
ድም ፡ ዘበጎደለ ፡ መለኮቱ ፡ በመለኮታዊ፡
ሥልጣኑ ፡ አንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ብሎ ፡
ሕገጋተ፡ወንጌልን፡የሠራልን፡(ጥቅ)፡ከመ፡
በሰሉ ፡ ዚአነ ፡ ኃይሉ ፡ ወመለኮቱ ፡ ወአ
ምልኮቱ ፡ እንተ ፡ ተውህበት ፡ ለነ ፡ የሚ
ል ፡ አብነት ፡ ይገኛል ። (ዘይወስድ) ፡ ወደ
ሕይወት ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚወስድ ፡ አለ
ሕይወት ፡ ሐይው ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡
ነው ፡ (ጽድቅ) ፡ ትሩፋት ፡ ነው ፡ (ወኢቱ፡
ዘጸውዐነ፡ (ሠናይት) ፡ ጽማዌ፡ (ስብሐት)፡
ከዊነ ፡ እሳት ፡ ነው ፡ ይሽውም ፡ እኛን ፡
ከጽማዌ ፡ እስከ ፡ ከዊነ ፡ እሳት ፡ ያደረሰ
በት ። ሐተታ ፡ ስብሐት ፡ አለው ፡ ከዊነ ፡
እሳትን ፡ ከዚህ ፡ መሳርግ ፡ ሲደርሱ ፡
ነጽሮተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡ (በዘ
ቦቱ ፡ ነሐዩ) ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደን ፡
በምንኖር ፡ ገንዘብ ፡ (ወነዐቢ) ፡ ድል ፡
በምንነሣ ፡ ገንዘብ ፡ (ወንክብር) ፡ በምን
ከብር ፡ ገንዘብ ፡ (በተስፋሁ) ፡ ነዐቢ ፡ ላለ
ው ፡ ጽንኡ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ሞእክዎ ፡ ለዓ
ለም ፡ ብሎ ፡ በነገረን ፡ ተስፋ ፡ ድል ፡ በም
ንነሣ ፡ ገንዘብ ፡ ከዚህ ፡ መሳርግ ፡ ሲደ
ርሱ ፡ አይዋጋቸውምና ። አንድም ፡ (ንክ
ብር) ፡ በምንከብር ፡ ገንዘብ ፡ (ወነዐቢ) ፡
ልዕልና ፡ ነፍስን ፡ በምናገኝ ፡ ገንዘብ ፡
(ዐተስፋሁ) ፡ ነዐቢ ፡ ላለው ፡ ወዘሰ ፡ ከ
መዝ ፡ ይሚሀር ፡ ለሰብእ ፡ ውኡቱ ፡ ዐ
ቢያ ፡ ይከውን ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
ብሎ ፡ በነገረን ፡ ተስፋ ፡ ልዕልና ፡ ነፍስን፡
በምናገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ጸውዐነ ፡ ላለው ፡
ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ማንሻ ፡ ነው ። አን
ድም ፡ በተስፋሁ ፡ የዐርፍ ፡ ነምር ፡
ምስለ ፡ ጠሊ ፡ ወተኵላ ፡ ምስለ ፡ በግዕ ፡
ብሎ ፡ ባናገረው ፡ ተስፋ ፡ ክብሩን ፡ ለመ
ውረስ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡
(ጥቅ) ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ መለክዋ ፡ በር
ስት ፡ መለኮታዊት ፡ እንዲል ። ወአንት
ሙኒ ፡ በሱሉ ፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ እናንተም፡
አጥፊ ፡ የሚሆን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ፈቃድ
እየሸሻችሁ ፡ እየራቃችሁ ፡ በውስጥ ፡
በአፍአ ፡ ችኮላን ፡ አድርጋችሁ ፡ በሃይ
ማኖት ፡ ላይ ፡ ጽማዌን ፡ ያዙ ፡ ይህ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ያንድነት ፡ የሦስትነት ፡ አይደ
ለም ፡ ይደረግልኛል ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡

ገድል ፡ የመግባት ፡ ነው ፡ (ታሪክ) ፡ እንደ
፪ ፡ አኀው ፡ ፩ ፡ ጸዋሚ ፡ ተሐራሚ ፡ ዝጉ
ሐዊ ፡ ባሕታዊ ፡ ነው ፡ ፩ ፡ አሆ ፡ በሀለ ፡
ተአዛዚ ፡ ጐር ፡ ላእክ ፡ ነው ፡ ሁሉም፡ በቅ
ተዋል ፡ የሁንንም ፡ መብቃት ፡ ማኅበሩ ፡
ያውቃሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ፡ ባሕታዊ፡ ይበ
ልጥን ፡ወይስ፡ ይህ፡ ረድኡ፡ይበልጥ፡ ሲበባ
ሉ፡ አበ፡ ማኅበሩ፡ በጸጋ፡ ተገልጸለት ፡ አን
ተ፡ ባሕታዊ ፡ አንተም ፡ ረድኡ፡ ሁናችሁ ፡
ለበዓል፡ የምንሳዘንዘው፡ ቀጤማ ፡አምጡ፡
ብሎ ፡ ሐርገጻት ፡ ካሉበት ፡ ባሕር ፡ ሰ
ደዳቸው ፡ ያ ፡ ረድኡ ፡ ሐርገጻትን ፡ እየጠ
ቀጠቀ ፡ እየተራመደ ፡ ገብቶ ፡ ከመካከል ፡
ይነቅል ፡ ገሮመር ፤ ያ ፡ ዝጉሐዊ ፡ ባሕታ
ዊ ፡ ከዳር ፡ ቁሞ ፡ ቀረ ፡ ወንድሜ ፡ ገብተ
ህ ፡ ከመካከል ፡ አትነቅልምን ፡ አለው ፡
ጎድጒኒ፡ አ ፡ እጐየ ፡ እስመ ፡ ዓዲ፡ ኢቆም
ኩ ፡ ውስተ ፡ መሳርገ ፡ ሃይማኖትክ ፡ ብሎ
ታል ፡ ኢዐረጉ፡ ኢበጸሕኩ፡ ሲል፡ ነው ፡
በዚህ ፡ አውቀዋል ፡ ከዚህ ፡ መሳርግ ፡ ሲ
ደርሱ ፡ መላእክትን ፡ ሲወጡ ፡ ሲወርዱ ፡
ያያሉ ፡ የሚወጡበትን፡ የሚወርዱበትን ፡
ምክንያት ፡ ግን ፡ አያውቁትም ፡ ዋጋ ፡ ያ
ልያዘ ፡ ሰው ፡ ገበያ ፡ ወጥቶ፡ ዋጋ ፡ ሳያደር
ግ ፡ እንዲመለስ ። ታሪክ ፡ እንደ ፡ ባለ ፡
አሰፈሬድ ፡ (እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊር) ፡
ከገበያ ፡ ተቀምጦ ፡ እንቅብ ፡ ዶርዶሮ ፡
ሲሸጥ ፡ ባለ ፡ እንቅብ ፡ ዋጋ ፡ ንገር ፡ አ
ለው ፤ ሚካኤልኑ ፡ የወቢ ፡ ወሚመ ፡ ገብ
ርኤል ፡ አለው ፡ ምን ፡ አልህ ፡ ቢሉው ፡
ደንግጦ ፡ ከነሁሉም ፡ ጥሎለት ፡ ሄዲል ፡
(ወበሣኔይት ፡ ለአእምሮ) ፡ በጽማዌም ፡
ላይ ፡ ልባዌን ፡ ያዙ ። ሐተታ ፡ ከዚህ ፡
መሳርግ ፡ ሲደርሱ ፡ መላእክት ፡ ሲወጡ ፡
ሲወርዱ ፡ ያያሉ ፡ የሚወጡበትን ፡ የሚ
ወርዱበትንም፡ ምክንያት፡ ያውቃሉ፡ዋጋ፡
የያዘ ፡ ሰው ፡ ከገበያ ፡ ገብቶ ፡ ዋጋ ፡ አድ
ርጎ ፡ እንዲመለስ ፡ (ወበአእምሮ ፡ ለኢዘ
ምዎ) ፡ በልባዌም፡ ላይ፡ ጣዕመ፡ ዝማሬን ፡
ያዙ ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ ለውዳሴኒ ፡ ከንቱ ፡
ይልእካ ፡ ዝሙት ፡ እንዲል ። ከዚህ ፡ መ
ዓርግ ፡ ሲደርሱ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይቃ
ወማቸዋልና ፡ (ወበኢዘምዎ ፡ ለትዕግሥ
ት) ፡ በጣዕመ ፡ ዝማሬም ፡ ላይ ፡ አንብዓ፡
ንስሓን ፡ ያዙ ፡ ከዚህ ፡ መሳርግ ፡ ሲደ
ርሱ ፡ ሳይሰቀቁ ፡ እንባቸው ፡ እንደ ፡ ኩ
ስኩስት ፡ ውኃ ፡ ይፈሳል ፡ (ወበትእግሥ
ት ፡ ለአምልኮ)፡ በአንብዓ፡ ንስሓም፡ ላይ ፡
ሁነኔን ፡ ውቃቤን ፡ ያዙ ፡ ሁነኔ ፡ ሥጋን ፡
ለነፍስ ፡ ማስገዛት ፡ ነው ፡ ውቃቤ ፡ በዚያ
ው ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ ውቃቤ ፡ ጥገኛ ፡
ሁነኔ ፡ መደበኛ ፡ ወበአምልኮ፡ ለተአኅዎ፡
በሁነኔ ፡ በውቃቤም፡ ላይ፡ ንጹሬን፡ ሁሰት
ን ፡ ያዙ ፤ ንጹሬ ፡ ካሉበት ፡ ሆኖ ፡ መላእ
ክትን ፡ በየከተማቸው ፡ ማየት ፡ ነው ፡ ሁ
ሰት ፡ እንደ ፡ እግረ ፡ ፀሓይ ፡ ከሁሉ ፡ መ
ድረስ ፡ ነው ፤ ወበተአኅዎ ፡ ለተፋቅሮ ፡
በሁሰት ፡ በንጹሬም ፡ ላይ፡ ተሰጥሞን፡ ፍ
ቅረ ፡ ደቂቀ ፡ እንለ ፡ እመሕያውን ፡ ያዙ ፡
ተሰጥሞ ፡ ገባሐረ ፡ ብርሃን ፡ መዋኘት ፡
ፍቅር ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡
ባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ሳይሉ ፡ ሁሉን ፡ አስተካ
ክሎ ፡ መውደድ፡ ነው ፡ (ወዝንቱ ፡ ኩሉ)፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ካለ ፡ ተር
ታ ፡ አትባሉም ፡ (ወኢኮንክሙ) ፡ ያለ ፡
ፍሬ ፡ ክብርም ፡ አላችሁ ፡ አትባሉም፡ ለነ
ጽሮተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ያበቃችኋል ፡
እንጅ ፡ ከዚህ ፡ መሳርግ ፡ ሲደርሱ ፡ ከዊነ፡
እሳት ፡ ነጽሮተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና።
፱ ፤ ወዘሰ ፡ ኢሀሎ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ምግባር ፡ ዕ
ውር ፡ ውእቱ ፡ ዘየሐውር ፡ በመርሰስ ፡
በዚህ ፡ ምግባር ፡ የሌለ ፡ ግን ፡ በዳሰሳ ፡ እ
ንደሚሄድ ፡ ዕውር ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወረሰወ ፡ አንጽሖ ፡ ርእሶ ፡ እምእለ ፡ በልያ ፡ በላዕሌሁ ፡ ኃጣውኢሁ ።

አንጽሖ ፡ ርእሱ ፡ አንጽሖ ፡ ርእሶ ፡ ይላል ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ከዘገዩበት ፡ ኃጣውኢ ፡ ራሱን ፡ ከማንጻት ፡ የዘነጋ ፡ ነው ። ሐተታ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ቢሉ ፡ ልብሱ ፡ ከውቃ ፡ ወድቆበት ፡ ውኃው ፡ እንዶዱ ፡ ሳለ ፡ የማያጥበውን ፡ ቤቱ ፡ ፈርሶበት ፡ ዕንጨቱ ፡ ሣሩ ፡ ሳለ ፡ የማይሠራውን ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ይመስላል ፡ (ግዋም) ፡ ኃጣውኢሁ ፡ በላዕሌሁ ፡ ፩ ፡ የሐ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ፲፭።

፲ ፤ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ጐኦሉ ፡

አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ፡

ከመ ፡ በጽንዐ ፡ ምግባሪክሙ ፡ ጽንዕተ ፡ ትኩን ፡ ጽዋዔክሙ ፡

በሥራችሁ ፡ መረዳት ፡ በሃይማኖት ፡ ንዑ ። ትልዉኒ ፡ ተብላችሁ ። አንድም ፡ በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብላችሁ ። አንድም ፡ ኃላ ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ቡሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ ተብላችሁ ፡ የምትጠሯት ፡ አጠራር ፡ የጸናች ፡ የተረዳች ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡

ወታወፍዩ ፡ ሐሳበክሙ ፡

የሃይማኖታችሁ ፡ ግምገማ ፡ ምግባራችሁን ፡ ታበረክቱ ፡ ዘንድ ፡ ጐኦሉ ፡ ላለው ። ሐተታ ፡ ምግባርን ፡ የሃይማኖት ፡ ግምገማ ፡ አለው ፡ አምነው ፡ የሚሠሩት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትገብሩ ፡ ኢትስሕቱ ።

ይህንም ፡ ስትሠሩ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ትንግኤ ፡ ሙታን ፡ ኀልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የለም ፡ አትበሉ ። አንድም ፡ አትታበዩ ። አንድም ፡ ገድል ፡ አትወስኑ ።

፲፩ ፤ ወይትመሀበክሙ ፡ ርኁብ ፡ ፍኖት ።

ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ባትሉ ፡ ሃይማኖተ ፡ ርእይ ፡ ይሰጣችኋል ። አንድም ፡ ባትታበዩ ፡ ውሳጣዊ ፡ ትሕትና ፡ ይሰጣችኋል። አንድም፡ ገድል፡ባትወስኑ፡እንበለ፡ጸእር፡ የሚሠራ ፡ ሥራ፡ ይሰጣችኋል፡ (ዋቅ) ፡ እስመ ፡ ዘይዌስን ፡ ገድለ ፡ ለርእሱ ፡ ይመስል ፡ ብእሴ ፡ ዘየኀድር ፡ ቤተ ፡ ፈቂር ፡ እንዲል ። ሐተታ ፡ ቅዱሳን ፡ ከበቁ ፡ በኋላ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አያውቁትም ፡ እንደ ፡ አባ ፡ በትረ ፡ ማርያም ፡ ሥራውን ፡ እየሠሩ ፡ እንደ ፡ እንዝርት ፡ ራስ ፡ ይዞሩ ፡ ነበር ፡

ዘይወስድ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ።

ወመንግሥቱ ፡ ለመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ጌትነቱን ፡ ወደ ፡ መውረስ ። አንድም ፡ በመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ለመኖር ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚያደርስ ።

፲፪ ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ እጽህቅ ፡ ለክሙ ፡ ዘልፈ ፡ ወአዘክረክሙ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡

ስለዚህም ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ላሳስባችሁ ፡ እወዳለሁ ፡

እንዘ ፡ ጽኑዓን ፡ አንትሙ ፡ በዘሀለወ ፡ ጽድቅ ፡

በተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ በተሠራላችሁ ፡ ሥርዐት ፡ ጸንታችሁ ፡ ሳላችሁ ፡ (ጥቅ) ፡ ወድሰ ፡ ለሰብእ ፡ በዘኢኮነ ፡ ድልወቱ ፡ እስመ ፡ ሰብሐ ፡ ለሰብእ ፡ ይዌስኮ ፡ ኃይለ ፡ እንዲል ፡ እንዘ ፡ ጽኑዓን ፡ አንትሙ ፡ አለ ፡ ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።


፲፫ ፤ ወይመስለኒሰ ፡ ከመ ፡ ርቱዕ ፡ ሊተ ፡ አምጣነ ፡ ሀሎኩ ፡ በዝንቱ ፡ ሥጋየ ፡ አንቅሀክሙ ፡ በዘክሮ ፡

በተማርነው ፡ ትምህርት ፡ በተሠራው ፡ ሥርዐት ፡ ጸንተን ፡ ካለን ፡ ምን ፡ ትለናለህ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ በሕይወተ ፡

ሥጋዬ ፡ ሳለሁ ፡ ኀልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ትንግኤ ፡ ሙታን ፡ እንዳለ ፡ በማሳሰብ ፡ ላነቃቃችሁ ፡ የሚገባኝ ፡ ይመስለኛል ። ሐተታ ፡ በሬ ፡ ሲሰብ ፡ ጅራፍ ፡ ፈረስ ፡ ሲጋልብ ፡ አለንጋ ፡ እንዲያጮሁበት ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፭ ።

፲፬ ፤ እስመ ፡ አእምር ፡ ከመ ፡ ፍጥንት ፡ ይእቲ ፤ ስሳሌ ፡ ዚአየ ፡ እምኔክሙ ፡ በከመ ፡ አይድዐኒ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ከናንት ፡ በሞት ፡ መለየቴ ፡ ፈጥና ፡ እንደ ፡ ደረሰች ፡ አውቃለሁና ፡ ፍጡነም ፡ ይላል ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ነገረኝ ። ሐተታ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነግሮታል ፡ ቢሉ ፡ እመጽእ ፡ ግብተ ፡ ከመ ፡ ሠራቂ ፡ መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ ለሁሉ ፡ ነውና ። አንድም ፡ በቁሙ ፡ ታይቶ ፡ ነግሮታል ፡ ታሪክ ፡ አልታብዮስ ፡ አክርጳስ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ መኳንንት ፡ ሮም ፡ ነበሩ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከዚህ ፡ ዓብቶ ፡ ብፁዓን ፡ ንጹሓነ ፡ ልብ ፡ እያለ ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ ምሽቶቻቸው ፡ እንደረስባችሁ ፡ ቢሏቸው ፡ አይሆንም ፡ አሏቸው ፤ ምሽቶቻችን ፡ ያልታዘዙልን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁ ፡ እናንተ ፡ እንጅ ፡ በሌላችሁበት ፡ ጊዜ ፡ እየገባ ፡ የሚያስተምራቸው ፡ አለ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ፤ ይህማ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እሱንስ ፡ እንገለዋለን ፡ ብለው ፡ መከሩ ፡ ምሽቶቻቸው ፡ ይህን፡ ሰምተው፡ በፈሊጥ፡ ያሰናብቱታል፡ ተክልና፡ ቡቃያ፡ ዝናም፡ ሲበዛበት፡ ችክ ፡ ብሎ ፡ ይቀራል ፡ እኛም ፡ ትምህርት ፡ ሲበዛብን ፡ እንሰለቻለንና ፡ አባታችን፡ ወጠኸልን ፡ ሰንብት ፡ አሉት ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ነገሩት ፡ ወወለጠ ፡ አስኬማሁ ፡ ይላል ፡ ልብሱን ፡ ለውጠ ፡ ሲወጣ ፡ ጌታ ፡ መስ



ወተሰቅለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቍልቍሊተ ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀሉን ፡ ተሸክሞ፡ በአንቀጸ፡ ሮም፡ ታየው፡ አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይ ደለህምን ፡ አለው ፡ አምን ፡ አለው ። በክ መ ፡ ተሰቀልክ ፡ ቅድመ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዳግመኛ፡ትሰቀል፡በሮም፡አለው፡ አንተም ፡ ፈራህ ፡ ምን ፡ ላድርግ፡ አለው፡ ተሰቀል ፡ እንጅ ፡ ሲለኝ ፡ ነው ። ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ (ወአስተብቊዖሙ ፡ ከመ ፡ ይስ ቅልዎ፡ቊልቊሊተ፡ይላል)፡እንደ፡ጌታዬ ፡ ሽቅብ፡ አትስቀሉኝ፡ ዘቅዝቃችሁ ፡ ስቀ ሉኝ ፡ ብሎ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሙታልና ፡ በከመ፡ አይድዐኒ ፡ እግዚአየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ አለ ፡ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፲፰-፲፱ ።

፲፭ ፤ ወዓዲ ፡ ጕጕኤ ፡ ከመ ፡ ተሀሉ ፡ ኅቤክሙ ፡ ዘቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘልፈ ፡

ይህች፡ ትእዛዝ ፡ ሁል ፡ ጊዜ፡ በናንተ ፡ ጸን ታ፡ትኖር ፡ዘንድ ፡ አለ ፡ ሠራሚ ፡ መጋቢ ፡ ትንግሌ ፡ ሙታን ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ አለ ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ፡

ወከመ ፡ ትዘክርዋ ፡ እምድኅረ ፡ ኅልፈትየ ፡

ከሞትሁም ፡ በኋላ ፡ ታስብዋት ፡ ዘንድ ፡

ወከማሁ ፡ ትግበሩ ።

እንዲህ ፡ ስለ ፡ አልኋችሁም ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አስቦ ፡ መቅረት ፡ አይረባምና ፡ ትግበሩ ፡ አለ ።

፲፮ ፡ አስመ ፡ ኢኮነ ፡ መኃደምተ ፡ ጥበብ ፡ ዘተ ሰመነ ፡

ተረት ፡ አሪትን ፡ የምናስተምር ፡ አይደለ ንምና ። አንድም ፡ የምናስተምረው ፡ ተረ ት ፡ አሪት ፡ አይደለምና ። ሐተታ ፡ ትረ ት ፡ አላት ፡ አሪትን ፡ ተረት ፡ የራት ፡ መ ቆያ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሪትም ፡ የወንጌል ፡ መቆያ ፡ ሆና ፡ ተሠርታለችና ፡ ጥበብ ፡ አላት ፡ ከተርታው ፡ ነባር ፡ ሲለይ ፡

ወአመርናከሙ ፡ ቦቱ ፡ ኀይሎ ፡ ለእግዚእነ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወምጽአቶ ፡ ወሀልዎቶ ።

(ሀልዎቶ) ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ መኖሩን ፡ (ኀይሎ) ፡ አ ምጻኤ ፡ ዓለማትነቱን ፡ (ምጽአቶ) ፡ በሥ ጋ ፡ መምጣቱን ፡ በአሪት ፡ የነገርናችሁ ፡ አይደለምና ፡ ኢተሰነ ፡ ላለው። አንድም፡ (ምጽአቶ) ፡ በሥጋ፡ መምጣቱን፡(ኀይሎ)፡ በኀቱም ፡ ድንግልና ፡ መወለዱን ፡ በኀ ቱም ፡ ድንግልና ፡ መፀነሱን ፡ (ሀልዎቶ) ፡ በዚህ፡ዓለም፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከሦስ ት፡ ወር፡ መኖሩን። አንድም፡ (ምጽአቶ)፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ለማሳለፍ ፡ መምጣቱን ፡ (ኀይሎ) ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ማሳለፉን ፡ (ሀል ዎቶ) ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አሳልፎ ፡ መኖሩን፡ በአሪት ፡ የነገርናችሁ ፡ ያስተማርናችሁ ፡ አይደለምና ። ሐተታ ፡ ምነው ፡ በአሪት ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ይል ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በአሪት ፡ ሆነን ፡ የነገርናችሁ ፡ አይደለምና ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ ዓበይተ ፡ ነ ቢያት ፡ የነገርናችሁ ፡ አይደለምና ፡ እኛ ፡ ከዘመኑ ፡ ደርሰን ፡ መልኩን ፡ አይተን ፡ አብረን ፡ ወጥተን ፡ ወርደን ፡ ነገርናችሁ ፡ እንጅ ። አንድም ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ሙሴ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ሳሙኤል ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አልነገርናች ሁምና ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሠርተን ፡ በቅተን ፡ ከመዓርገ ፡ ነጽሮ ፡ ደርሰን ፡ ነ ገርናችሁ ፡ እንጅ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፲፯ ፤ ዘነሥአ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ክብረ ፡ ወልዕልና ፡ ወስብሐተ ።

ከእግዚአብሔርነቱ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ ያደ ረገውን ፡ ፍጹም ፡ ክብሩን ፡ አይተን ፡ ነገ

ርናችሁ ፡ እንጅ ፡ በአርአያሁ ፡ ተከዊነ ፡ ወበአምሳሊሁ ፡ ተመሲለ ፡ የሚል ፡ አብ ነት ፡ ይገኛል ፡

ወቃል ፡ ዘወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡

ሎቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ዘምሉእ ፡ ስብሐተ ፡ ወልዕልና ፡

ለሱ ፡ የተነገረለት ፡ ክብርን ፡ ልዕልናን ፡ የተመላ ፡ ቃል ፡

ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ ዘአነ ፡ ኀረይኩ ።

በሱ ፡ ሕልው ፡ ሁኜ ፡ ልመለክበት ፡ ለመ ሥዋዕትነት ፡ የመረጥሁት ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ና ፡ ፲፯ ፡ ፭ ። ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፴፭ ። ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

፲፰ ፤ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ ንሕነ ፡ ሰማዕናሁ ፡ ከመ ፡ እም ሰማይ ፡ ወረደ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ሀሎን ፡ ምስሌሁ ፡ በደ ብረ ፡ ሙቅደሱ ፡

ሰማዕነ ፡ ሎቱ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከወደ ፡ ሰማይ፡ ለሱ ፡ እንደ ፡ ተነገረለት ፡ ሰማን ፡ ጌትነቱ ፡ ከሙሴ ፡ ከኤልያስ ፡ ተለይቶ ፡ በታወቀበት ፡ አምልኮቱ ፡ በል በ ፡ ሐዋርያት ፡ በጸናበት ፡ በልበ ፡ ሐዋ ርያት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ በነሣበት ፡ ምሳሌው ፡ በተፈጸመበት ፡ በአብርሃም ፡ ጉልት ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ከሱ ፡ ኃራ፡ ሳለን ፡ ሰማንለት ። ሐተታ ፡ አብርሃምን ፡ መቅደስ ፡ አለው ፡ ማኅደረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ።

፲፱ ፤ ወብነ ፡ ዓዲ ፡ ዘአምዝኒ ፡ ይቀድም ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ዘያዐውቅ ፡ ዘንተ ፡

ለመምሕሩ ፡ አይረዳ ፡ ከባሕር ፡ አይቀዳ ፡ የለምና ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ አለ ው ፡ ትላለህ ፡ እንጅ ፡ ማን ፡ ያውቅልሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ የሚቀድም ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡

የነቢያት ፡ ቃል ፡ አለላችሁ ፡ መኑ ፡ ስሙ፡ ወመኑ ፡ ስመ ፡ ወልዱ ፡ ለመሚሑ ፡ ለ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድየ ፡ አንተ ፡ ወእነ ፡ የም ፡ ወለድኩከ ፡ እነ ፡ እከውኖ ፡ አባሁ ፡ ወውእቱ ፡ ይከውንኒ ፡ ወልድየ ፡ ሕፃን ፡ ተወልደ ፡ ለነ ፡ ወልድ ፡ ተውህበ ፡ ለነ ፡ ለሊሁ ፡ ኢያሱስ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ያለው ። ሐተታ ፡ ነቢያት ፡ ቢል ፡ የተመቸ ፡ ነቢይ ፡ ቢል ፡ ያንድ ፡ ገንዘብ ፡ ሽሕ ፡ ያላገብ ፡ እንዲሉ ፡ ነቢይ፡ የሁሉ ፡ ነውና ፡

ወእምከመ ፡ ጥቀ ፡ ታሜንዩ ፡ ገብረ ፡ ወትኔጽርዎ ።

በአንብቦ ፡ መጻሕፍት ፡ ጽሙዳን ፡ ብት ሆኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ብትመለከቱ ፡

ይከውን ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ማኅቶት ፡ እንተ ፡ ታበርህ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ጽልመት ፡

በጨለማ ፡ ቦታ ፡ እንደሚያበራ ፡ ፋና ፡ ይሆንላችኋል ፡

እስከ ፡ ታበርህ ፡ ለክሙ ፡ ዕለት ፡

ፀሓይ ፡ እስኪያበራላችሁ ፡ ድረስ ፡ (ጥቅ) ፡ ወበትእዛዝከ ፡ ይቀውም ፡ ዕለት ፡ እንዲል ።

ወይሠርቅ ፡ ለክሙ ፡ ዜዝ ፡ ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ ዘያበርህ ።

ያጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ እስኪወጣላችሁ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ምስጢር ፡ ሂዶ ፡ ዘበያርህ ፡ አለ ። አ ንድም ፡ (ዕለት) ፡ ሥጋዊ ፡ እስትትገለጽ ላችሁ ፡ ድረስ ፡ (ዜዝ) ፡ አእምሮ ፡ መንፈ ሳዊ ፡ በልቡናችሁ ፡ እስኪሳልባችሁ ፡ ድረስ ። አንድም ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚ አብሔር ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ ዓበይተ ፡ ነቢያት ፡ አልነገርናችሁም ፡ ከዘመኑ ፡ ደርሰን ፡ መልኩን ፡ አይተን ፡ አብረን ፡ ወጥተን ፡ ወርደን ፡ ነገርናችሁ ፡ ትላለህ ፡ እንጅ ፡ ማየትህን ፡ ማን ፡ ያውቅልሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንስ ፡ የሚያስ ረዳ፡ከዚህ፡የሚበልጥ፡የነቢያት፡ ቃል፡ አለ

www.ethiopianorthodox.org

ላችሁ ፤ ውእተ፡ አሚረ፡ ይሠርቅ፡ ፀሓየ ፡ ጽድቅ፡ ወሕይወት፡ ታሕተ ፡ ክነፊሁ ፡ ያለው። ሐተታ፡ነቢይ፡ ቢል፡ የተመቸ፡ ነቢያት፡ ቢል፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡ ካልጠራ ፡ ማብዛት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ (ወእምከመ ፡ ጥቀ) ፡ ከጊዜው ፡ ብትደርሱ ፡ አብራችሁ፡ ብትወጡ፡ ብትወርዱ ፡ (ወትኔጽርዎ)፤ መልኩን ፡ ብታዩ ፡ (ይከውን ፡ ለክሙ) ፡ በጨለማ ፡ ቦታ ፡ እንደሚያበራ ፡ ፋና ፡ ይ ሆንላችኋል፡(እስከ፡ታበርህ) ፡ዕለተ፡ዐርብ፡ እስትትገለጽላችሁ፡ ድረስ ፡ (ወይሠርቅ) ፡ ቤዝ፡ክርስቶስ፡በልቡናችሁ፡ እስኪያድርባችሁ፡ድረስ ። አንድም፡ከመዝ፡ይቤ፡ሙሴ፡ ከመዝ ፡ ይቤ፡ ሳሙኤል ፡ እንደሚሉ ፡ እን ደ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አልነገርናችሁ ም ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሠርተን ፡ ከመ ፡ ዓርገ፡ ነጽሮ፡ ደርሰን ፡ በቅተን፡ ነገርናችሁ፡ ትላለህ ፡ እንጅ ፡ መብቃትህን ፡ ማን ፡ ያውቅልሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ንስ ፡ የሚያስረዳ ፡ የሚያሳውቅ ፡ የነቢ ያት ፡ ቃል ፡ አለላችሁ ፤ (ነቢያት ፡ የተና ገሩት ፡ ቃልም ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ሕዝቅኤል ፡ በሦስት ፡ ጎበር ፡ የተሠራች፡ አዳራሽ ፡ አይታል ፡ በጎብረ ፡ ማይ ፡ በጎ ብረ ፡ ሰማይ ፡ በጎብረ ፡ በረድ ፡ ንጉሥ ፡ ከላይዋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠባት ፡ ጎብረ ፡ማ ይና ፡ ጎብረ ፡ በረድስ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጎብረ ፡ ባሕርይ ፡ ም ሳሌ ፡ ነው ፡ ንጉሥ ፡ የመንፈስ ፡ ቅ ዱስ ፡ አዳራሽ ፡ የሐዋርያት ፡ ሦስቱ ፡ ጎበር ፡ የንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ የንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ የንጽሐ ፡ ልቡና ፡ (ታሜንዩ) ፡ ከመም ሕረ ፡ ንስሓችሁ ፡ ብትጫወቱ ፡ (ወትኔ ጽርዎ)፡ አንቀጸ ፡ ንስሓን፡ ብትመለከቱ ፡ (ይከውን፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ማኅቶት)፡ በጨ ለማ፡ ቦታ፡ እንደምታበራ፡ፋና፡ይሆንላችኋ ል ፡ ዕለተ፡ ትንሣኤ፡ እስትትገለጽላችሁ ፡ ድረስ፡ አእምሮ፡ መንፈሳዊም፡እስኪፈጸም ላችሁ፡ ድረስ። ሐተታ፡ ነጋድያን፡ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ሲሄዱ ፡ ውለው ፡ ሌሊት፡ እን ዲያውን፡ዝም፡ብለን፡እናድራለን፡ ብለው ፡ ከአዝማደ፡አእባን፡ ከአዝማደ፡ ሐፃውንት ፡ ቡላድ ፡ መተው ፡ ሙብራት፡ አብርተው ፡ ሲሠሩ፡ ያድራሉ ፡ ሌሊት፡ የሠሩት፡ ቀን ፡ ከሠሩት ፡ ተካክሎ ፡ ዋጋ ፡ ያወጣላቸዋል ፡ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ውሉደ ፡ ሌሊት ፡ ነቢ ያት ፡ ከውሉደ ፡ መዓልት ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ ተካክለው ፡ ዋጋ ፡ ማግኘታቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ ከሰው ፡ የሚገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ በፋና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚ ገኘውን ፡ በፀሐይ፡መስለው፡ተናገረ፡ (ጥቅ)፡ ሃይማኖት፡እንተ፡ትጠረይ፡ እምተምህሮ ፡ ኢታግዕዞ ፡ ለሰብእ ፡ እምኑፋቄ ፡ ወእም ትሕዝብት ፡ እንዲል ፡ መዝ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፷ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፭ ፤ ወዘንተ ፡ ባሕቱ ፡ ቅድሙ ፡ አእምሮ ፡

ወብነ ፡ ዓዲ ፡ ዘእምዝኒ ፡ ይቀድም ፡ ቃለ ፡ ነቢያት፡ ዘያዐውቅ፡ ዘንተ፡ ብሎ፡ ነበረና ፡ ወዘንተ ፡ ባሕቱ ፡ አለ ፡ አስቀድሞ ፡ ይህ ን ፡ ብቻ ፡ ዕወቁ ፡

ከመ ፡ ኵሉ ፡ ተነብዮ ፡ ዘውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ አልቦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍካሬሁ ።

በመጽሐፍ ፡ ያለ ፡ ትንቢት ፡ በትንቢት ነቱ ፡ እንደሌለ ፡ ወጥዶለት ፡ እንዳለ ፡ ዕወቁ ፡ ትፀንስ ፡ የነበረው ፡ ፀንሰት ፡ ትወ ልድ ፡ የነበረው ፡ ወለደት ፡ ሆኖ ፡ እን ዳለ ፡ ዕወቁ ፡ ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፮ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

፳፩ ፤ ወኢይከውን ፡ ተነብዮ ፡ ግሙራ፡ እምፈቃደ ፡ ሰብእ ፡

ሰው ፡ ራሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ትንቢት ፡ ልና ገር ፡ ቢል ፡

ወኢእምሥምረተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

ሌላውም ፡ ተናገር ፡ ቢለው ፡ ትንቢት ፡ መናገር ፡ እንዳይሆንለት ፡ ዕወቁ ፡

አላ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነበቡ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰብእ ፡ ተ ፈኢሞሙ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘ ንድ ፡ ታዝዘው ፡ ተናግረዋል ፡ እንጅ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ፤ ወቦቱ ፡ ባሕቱ ፡ ሐሳውያን ፡ ነቢያት ፡ ማዕከለ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ አለ ፡ ሀለዉ ፡ ማእከለክሙ ፡ ወውስ ቱትከሙ ፡ አለ ፡ ሐሰተ ፡ ይሚሀሩ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ ሐ ሰትን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሐሰተኞች ፡ መም ህራን ፡ እንዳሉ ፡ ቀድሞም ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ነቢያትን ፡ የሚያሳብሉ ፡ በነቢ ያት ፡ የሚያብሉ ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህ ራን ፡ ነበሩ ፡ በኤርምያስ ፤ ጊዜ ፡ እለ ፡ ጳስኮር ፡ በአሞጽ ፡ ጊዜ ፡ አሜስያስ ፡ ካህ ን ፡ ቤቴል ፡ በሚክያስ ፡ ጊዜ ፡ ሴዶቅያስ ፡ ወልደ ፡ ካህናን ፡ በኤልያስ ፡ ጊዜ ፡ ስም ንት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰተ ፡ እንደ ፡ ነበሩ። አንድም ፡ ብሰው ፡ ያለ ፡ ትንቢት ፡ ከሰው ፡ እንዳይ ገኝ ፡ ዕወቁ ፡ (ጥቅ) ፡ ወኮንኩ ፡ መጽ ሐፎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወአእምር ፡ መጽሐፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ። አንድም ፡ በሰ ው ፡ ያለ ፡ ትርጓሜ ፡ ከሰው ፡ እንዳ ይገኝ፡ ዕወቁ፤ ራሱ፡ በፈቃዱ፡ ልተርጕም፡ ቢል ፡ ሰውም ፡ ተርጕም ፡ ቢለው፡ እንዳ ይሆንለት ፡ ዕወቁ ፡ ቅዱሳን ፡ ሊቃውንት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጸላቸው ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ታዝዘው ፡ ተርጕመዋል ፡ እንጅ ። አንድም ፡ በኮር ፡ ላይ ፡ ኮር ፡ በጦ ር ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ እንዳይሰር ፡ እኛ ፡ አለ ፡ ብለን ፡ በምናስተምረው ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ የቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ የለም ፡ ማለት ፡ እንዳይኖር ፡ ዕወቁ ። አንድም ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ዐዘቅት ፡ ንጽፍት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዕወቁ ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ትንቢት ፡ ልናገር ፡ ቢለው ፡ ማስተማር ፡ እንዳይሆንለት ፡ ዕወቁ ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ተገልጸላቸው፡ አስተማሩ ፡ እንጅ ፡ ከመ ፡ በ ፡ ሐሳውያን ፡ ነቢያት ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ቀድሞ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ዛሬም ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ ሐሰትን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ አሉ ፡

ወእለ ፡ ካሕደ ፡ ያበውኡ ፡ ለሕርትምና ፡

ጥፋት ፡ ሊሆንባቸው ። አንድም ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣባቸው ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ክህደ ትን ፡ የሚያሳድሩ ።

ወይክሕድዎ ፡ ለእግዚአሙ ፡ ዘተሣየጠሙ ፡ በደሙ፡

በወርቀ ፡ ደሙ ፡ የዋጃቸው ፡ ፈጣሪያቸ ውን ፡ የሚክዱ ፡

ወያመጽእዋ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ፍጡነ ፡ ለሙስና ፡ ወለተ ሠርዎ ።

ጥፋትን ፡ መነቀልን ፡ በራሳቸው ፡ ፈጥ ነው ፡ የሚያመጡ ፡ መተከልን ፡ መደብ ፡ አድርጎላቸው ፡ መነቀልን ፡ የሚያመጡ ፡ አለ ፡ ሚቴ ፡ ፳፬ ። ፲፩ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፪ ፤ ወብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ይተልውዎሙ ፡ ለእሉ ፡ በእንተ ፡ ፍትወተ ፡ ዝሙቶሙ ፡

እሊህንም ፡ ዝሙታቸውን ፡ ስለ ፡ መው ደድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይመስሏቸዋል ፡ አለ፡ አብነት ፡ ያደርጓቸዋል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ ።

ሕገ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልን። አንድም ፡ ሕገ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌልን ፡ ይነቅፋሉ ። ሐተታ ጽድቅ ፡ አለው ፡ በግብሩ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፫ ፤ ወይትከሐዱ ፡ ቢቃል ፡ ዘለሊሆሙ ፡ ፈጠሩ ፡

ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ በተናገሩት ፡ ይከራከራሉ ፡ መከራከርማ ፡ እንዳይከራከሩን ፡ አለ ፡

ወቦቱ ፡ የሐውሩ ፡

በዚያው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ። አንድም ፡ በዚያው ፡ ተመርተው ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ይሄዳሉ ። አንድም ፡ ተፈጥሩ ፡ ይላል ፡ በተፈጠሩበት ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ይካዳሉ፤ በዚያውም ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ይባላሉ ፡ (ጥቅ) ፡ እንታክቲ ፡ ቃል ፡ እንተ ፡ ማረረ ታ ፡ በቀዳሚት ፡ ይእቲኪ ፡ ተሀውካ፤ በደኃሪት ፡ እንዲል ፡

ወደይኖሙሰ ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ እንተ ፡ ኢተዐርፍ ፡ ወሕርትምናሆሙ ፡ እንተ ፡ ኢትዴቅስ ።

ፍዳቸው፡ ጥፋታቸው ፡ ዓለም፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ የማያልፍ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነሡ ። አንድም ፡ ሳይጠፉ ፡ ውለው ፡ አድረው ፡ አያውቁም ። አንድም ፡ ፍዳቸው ፡ ዕዜው ፡ ዘኢይነውም ፡ እሳቱ ፡ ዘኢይጠፍዕ ፡ ያለ ው ፡ ነው ።

፬ ፤ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ ጥቀ ፡ እቢ ሶሙ ፡ ኢመሐለመ ።

ምነው ፡ እግዚአብሔር፡አያዘንላቸውምን፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ለመላእክትስ ፡ እንኳ ፡ አላዘነላቸውም ። ሐተታ ፡ ምነው ፡ መላ እክትስ ፡ እንኳ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ መላእክት ፡ የጥንት ፡ ፍጥረቶቹ ፡ ናቸውና ፡ የፊት ፡ ከብት ፡ የእጅ ፡ ወረት፡ እንዲሉ፡ በዚህስ ፡ አያዘንላቸውም፡ብሎ፡ እኛ፡ ግዙፋን፡ መላ እክት ፡ ረቂቃን ፡ እኛ ፡ ጎዳጣን ፡ መላእ ክት ፡ ብዙኃን ፡ እኛ ፡ ድኩማን ፡ መላእ ክት ፡ ኃያላን ፡ ናቸውና ፡ በዚህም ፡ አይ ደለ ፡ ብሎ ፡ ለመላእክት ፡ አብነት ፡ የላ ቸውም ፡ ለኛ ፡ ግን ፡ አለንና ፡ ለሰብአ ፡ ትካት ፡ መላእክት ፡ ለሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ለሚ ነሡ ፡ (ለምንነግ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ አብነት ፡ አሏቸውና ።

አላ ፡ ወደዮሙ ፡ ውስተ ፡ ጻዕረ ፡ ደይን ፡ ዘርሱን ፡

የሚነድ ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ባለበት፡ በገሃነም ፡ ጣላቸው ፡ እንጅ ፡

ወመጠዎሙ ፡ ይትኰነኑ ፡

ይቀጡ ፡ ዘንድ ፡ እሳቸውን ፡ ለፍዳው ፡ ፍዳውን ፡ ለሳቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡

ወይንበሩ ፡ ውስተ ፡ ጻዕረ ፡ ደይን ።

ጽኑዕ ፡ ሥቃይ ፡ ባለበት ፡ በገሃነም ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳ ፡ ቍ ፡ ፮ ።

፮ ፤ ወለዓለምኒ ፡ ቀደምት ፡ ኢመሐኮሙ ፡

ለቀደምት ፡ ለሰብአ፡ ትካትም ፡ አላዘነላቸውም ፡

አላ ፡ አትረፈ ፡ ሰማኒተ ፡ ነፍሰ ፡ ምስለ ፡ ኖኅ ፡

አትረፈ ፡ ምስለ ፡ ኖኅ ፡ ሰማኒተ ፡ ነፍሰ ፡ ምስለ ፡ ኖኅ ፡ ብለህ ፡ (ግጠም) ፡ ከኖኅ ፡ ጋራ ፡ ስምንት ፡ ሰዎች ፡ አስቀረ ፡ እንጅ ፡

ዘወቀባ ፡ ለጽድቅ ፡

ጽድቅን ፡ ከጠበቃት ፡ ከኖኅ ፡ ጋራ ፡

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዜናዌ ፡ በጽድቅ ፡

በ ፡ በግዕዝ ፡ ቦታ ፡ የገባ ፡ ነው ፡ ሃይማኖትን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ። ሐተታ ፡ ለማን ፡ ያስተምራል ፡ ቢሉ ፡ ለልጆቹ ፡ ልጆቹማ ፡ ተምረው ፡ አይደለም ፡ የዳኑ ፡

ቢሉ ፡ ለሌላው። አንድም ፡ አቤልሰ ፡ ኮነ ፡ ይትናገር ፡ በዜና ፡ እንዲል ፡ ነገሩ ፡ ጽንፍ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ደርሷል ፡ እስከ ፡ ምጽአት፡ ሲያያዝ ፡ ሲነገር ፡ ይኖራልና ፡

ወለባዕዳንሰ ፡ ሰብእ ፡ ረሲዓን ፡ ፈነወ ፡ አይኅ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

በሰብአ ፡ ትካት ፡ ግን ፡ ማየ ፡ ድምሳሴን ፡ ማየ ፡ ሥራዌን ፡ አዘዘባቸው ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፯ ። ዘፍጥ ፡ ፮ ፡ ፯፮ ።

፯ ፤ ወለአህጉረ ፡ ሰዶምኒ ፡ ወገሞራ ፡ አውዖን ፡ ወገፍትአን ፡

ሰዶም ፡ ገሞራ ፡ አዳማ ፡ ሱባማ ፡ ሲባዮ ንንም ፡ እንደ ፡ መቅሰፉ፡ቆላቸው ፡ እንደ ፡ ዓማ ፡ ገለበጣቸው ፡

ወከመዝ ፡ ኰነኖሙ ፡

እንዲህ ፡ ፈረደባቸው ። አንድም ፡ እያየ ፡ ነውና ፡ የሚጽፍ ፡ እንዲህ ፡ ፈረደባቸው ፡ ይላል ፡

ወአርአያ ፡ ረሰዮሙ ፡ ለእለ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ለኃጥአን ።

በኋላ ፡ ዘመን ፡ ለሚነሡ ፡ ኃጥአን ፡ አብነት ፡ አደረጋቸው ። ሐተታ ፡ አብነት ፡ ይሁኑ ፡ ብሎስ ፡ አያጠፋም ፡ ቸሸኖ፡ ብሎ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፱ ፡ ፳፬ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ።

፰ ፤ ወለጻድቅሰ ፡ ሎጥ ፡ ዘይትገፋዕ ፡ አምእለ ፡ ይኤብሱ ፡ በምግባረ ፡ ዝሙቶሙ ፡ አድጎኖ ፡

ዘይትገፋዕ ፡ እምእለ ፡ ይኤብሱ ፡ አድጎኖ ፡ እምእለ ፡ ይኤብሱ፡ ብለህ፡ ግጠም ፡ ዝሙትን ፡ በመሥራት ፡ ከሚበድሉ ፡ ሰዎች ፡ የሚበደል ፡ ሎጥን፡ ግን ፡ ከሚበ ድሉ ፡ ሰዎች ፡ ለይቶ ፡ አዳነው ፡

ወእንዘ ፡ ይሬኢ ፡ ወይሰምዕ ፡

ጻድቅ ፡ ሎጥ ፡ ይህን ፡ ሲያይ ፡ ሲሰማ ፡ አዳነው ።

፱ ፤ ወጎዳር ፡ ምስሌሆሙ ፡

ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲኖር ፡ አዳነው፡ ወዕለተ ፡ እምዕለት ፡ ሥጋንሻ ። አንድም ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲኖር ፡

ወዕለተ ፡ እምዕለት ፡ ያጼዕርዋ ፡ ለነፍሱ ፡ ጻድቅት ። በእከየ ፡ ምግባሮሙ ።

ከቀን ፡ በቀን ፡ እያሉ ፡ ጻድቅት ፡ ሰውነቱን ፡ በክፉ ፡ ግብራቸው ፡ ያስጨንቋት ፡ ነበር ፤ ብትመስል ፡ እኛን ፡ ምሰል ፡ ባት መስል ፡ ከሀገራችን ፡ ንቀል ፡ እያሉ፡መዝ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፶፮ ። ሕዝ ፡ ፬ ፡ ፬ ።

፲ ፤ ናቡኬ ፡ አእመርነ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክል ፡ አድኅኖቶሙ ፡ እምነ ፡ መንሱት ፡ ለጻድቃን ፡

እንኪያስ ፡ ወዳጆቹ ፡ ጻድቃንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያድናቸው ፡ አወቅነ ፡ (እናውቃለን ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ከሌለ ። ኖኅን ፡ ከድምሳሴ ፡ ሎጥን ፡ ከግፍታኢ ። ማን ፡ አዳነ ፡ ለማለት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡

ወለኃጥአንሰ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ ትጸንሖሙ ፡ ለተጽዕሮ።

ኃጥአንን ፡ ግን ፡ ጽኑ ፡ ፍዳ ፡ ለመቀበል ፡ የቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ትጠብቃቸዋለች፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ራእ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

፲ ፤ ወፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ ይተልዉዋ ፡ ድኅረ፱ ፡ ለፍትወቶሙ ፡

ይልቁንም ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋቸውን ፡ የሚከተሉትን ፡ አለ ፡ አብዝተው ፡ የሚሠሩትን ፡ የቍርፅ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ትጠብቃቸዋለች ፡

ወያንቆንዎ ፡ ለሥጋሆሙ ፡

ሰውነታቸውን ፡ በኃጢአት ፡ የሚያሳድፉትን ፡

ወያስተሐቅርዎ፡ ለፈጣሪሆሙ ፡

ፈጣሪያቸውን ፡ የሚነቅፉትን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጎቡላን ፡

ተካሮች ፡ ደፋሮች ፡

ወዝሉፋን ፡

ሴሰኞች ፡ ተሳዳቦች ፡ ኃጢአት ፡ አዘውታሪች ፡ ናቸው ፡

እለ ፡ ኢይደነግው ፡ ከመ ፡ ይፅርፉ ፡ ላዕለ ፡ ስብሐቲሁ ዘውእቱ ፡ ኀበ ፡ መላእክት ፡ ልዑላን ፡ እሙንቱ ፡ እም ኑሆሙ ፡ በኀይል ፡ ወበጽንዕ ።

እለ ፡ ልዑላን ፡ ወእለ ፡ኢይክሉ ፡ ብለሀ ፡ ግጠም ።

፲፩ ፤ ወኢይክሉ ፡ ተዐግሦ ፡ ከመ ፡ ያብጽሑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ደይን ፡ ዕርፈቶሙ ።

የስድባቸው ፡ ብድራት ፡ ፍዳቸውን ፡ ያመጡባቸው ፡ ዘንድ ፡ መታግሥ ፡ ከማይቻላቸው ፡ በኀይል ፡ በጽንዕ ፡ ከሳቸው ፡ በላይ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከመላእክት ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ ጌትነቱን ፡ ይነቅፉ ፡ ዘንድ ፡ ሲነቅፉ ፡ የማይደነግጡ ፡ ናቸው ፡ (ጥቅ) ፡ ወሰበ ፡ ሰምዐ ፡ ቃሎ ፡ መሪረ ፡ ለአርዮስ ፡ ርዕዱ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክት ፡ እንዲል ። አንድም እለ ፡ ኢይደነግጹ ፡ ወእለ ፡ ኢይክሉ ፡ብለሀ ፡ (ግጠም)፡ፍትሐ፡ ርቱዕ፡ ሥላሴ ፡ የስድባቸውን፡ ብድራት ፡ ፍዳቸውን፡ ያመጡባቸው፡ ዘንድ ፡ መታግሥ፡ የማይቻላቸው ፡ በኀይል፡ በጽንዕ፡ከሳቸው፡ በላይ፡ከሚሆኑ፡ ከመላእክት፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ ጌትነቱን ፡ ይነቅፉ ፡ ዘንድ ፡ ሲነቅፉ ፡የማይደነግጡ፡

፲፪ ፤ ውእቱመኬ ፡ ከመ ፡ እንስሳ ፡ ዘአልቦ ፡ ቃል ፡ ቃል ፡ እንዶሌለው ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ናቸው ፡ ቃልማ ፡ ምንዋ ፡ ተራራ ፡ የሚያናውጥ ፡ ብሎ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ዘይትወለድ ፡ ለሙስና ፡ ወለተሰርዎ ፡

ብርንዶው ፡ ለጥበስ ፡ ጥበሱ ፡ ለድቁስ ፡ እንደሚወለድ ፡ እንደሚፈጠር ፡

እሰመ ፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ ዘኢየአምሩ ፡ ለሕርትምና ሆሙ ፡

ጥፋት ፡ ሊመጣባቸው ፡ ጥፋት ፡ ሊሆንባቸው ፡ የማያውቁትን ፡ ጌትነቱን ፡ ይነቅፉና ፡

ወሎሙ ፡ በሙስናሆሙ ፡ አስበ ፡ ዓመፃ ።

በጥፉ ፡ በሐሰት ፡ ትምህርታቸው ፡ የዐመፅ ፡ ዋጋ ፡ አላቸው ፡ አለ ፡ አስተምረናል ፡ እያሉ ፡ ዋጋ ፡ ይቀበላሉ ። አንድም ፡ ዐስበ ፡ ዓማሚ ፡ ይላል ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚያመጣው ፡ ፍዳ ፡ አላቸው ፡ አንድም ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚቀበለውን ፡ ፍዳ ፡ ይቀበላሉ ፡ ኤር ፡ ፲፪ ፡ ፫ ። ይሁዳ ፡ ቁ ፡ ፲ ።

፲፫ ፤ ወያስተሐውዝዋ ፡ ለተደልዎ ፡ ስታየ ፡ ዕለቶሙ ፡

በዕለት ፡ መጠጣቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማድረግን ፡ አጣፍጠው ፡ የያዙ። አንድም ለተደልዎ ፡ ዕለተ ፡ ስታዮሙ ፡ መጠጣቸውን ፡ ባገኙባት ፡ ቀን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ማድረግን ፡ አጣፍጠው ፡ የያዙ ፡ ማክሰኞ ፡ ቢሆን ፡ ረቡዕ ፡ ኀሙስ ፡ ብናደር ገው ፡ ዐርብ ፡ ይከተለዋል ፡ ብለው ፡ ክቅዳሜ ፡ እስከ ፡ ረቡዕ ። አንድም ፡ ውስተ ፡ ስታየ ፡ ዕለቶሙ ፡ ይላል ፡ የዕለት ፡ መጠጣቸውን ፡ ባገኙባት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እየዘፈኑ፡ እያጨበጨቡ፡ አንወጣም ፡ ይላሉ ፡

ወይበልው ፡ እንዘ ፡ ሕብቁቃን ፡

እየሳቡ ፡ ይበላሉ ፡

ወርኩሳን ፡

ሠራዊ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ይላሉ ፡

እለ ፡ ኢይጸግቡ ፡

የማይጠግቡ ፡ ናቸው ። ሐተታ ፡ በልማድ ፡ እንዳይጠግቡ ፡ ይሳሳሉ ፡ እንዳያበረክትላቸውም፡ ሠራዊ፡ መጋቢ፡ የለም ፡ ይላሉና ፡

ወይትጐሐለዉ ፡ በፍቅሮሙ ፡

በፍቅራቸው ፡ ይከዳሉ ፡ አለ ፡ ሳይወዱ ፡ እንወዳችኋለን ፡ ይላሉ ፡

ወይትሜክሑ ፡ ለቢጾሙ ፡ ከመ ፡ ዘሠናይ ፡ ምግባሮሙ ፡

በጎ ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ አድርገው ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ይመካሉ ፡ እነገሌንማ፡እንጅ ፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡ እንዲህ ፡ አናገርናቸው ፡ ብለው ።

፲፱ ፤ ወምሉኣ ፡ ውስተ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ዝሙት ፡ ወኃጢአት ።

በዐይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ዝሙት ፡ ኃጢአት ፡ የተመላ ፡ ነው ። አንድም ፡ ምሉእ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ዝሙተ ፡ ወኃጢአተ) ፡ ዓይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ዝሙትን ፡ ኃጢአትን ፡ የተመላ ፡ ነው ፡

እንተ ፡ አልባቲ ፡ ዘይገሀግግ ፡

የሚያርቃት ፡ የሌለ፡ ዘያፈርሃ ፡ ዘያሴስላ ፡ ዘያርኅቃ ፡ ዘይከልኣ ፡ ዘያጎጽፃ ፡ ዘያደነግጻ ፡ ይላል ፡ የሐዋርያ ፡ እኩሌታ ፡ ይህነው ። ሐተታ ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ገላት ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፭ ።

ወያደነግፁ ፡ ነፍሰ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ስሑት ፡ ልቦሙ ፡

ልቡናቸው ፡ ቅርብ ፡ ቀረባ ፡ የሆነ ፡ ሰዎች ፡ ልቡናን ፡ ያሸብራሉ። አንድም ፡ ልቡናቸው ፡ እንደ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ እምብርት ፡ እንደ ፡ ተራራ ፡ ኮረብታ ፡ የሚሆን ፡ እሌሁ ፡ (ያደነግጹ) ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ያሸብራሉ ። ሐተታ ፡ ያግሬ ፡ ጋሻ ፡ እምብርት ፡ ቍና ፡ ጤፍ ፡ ቢያፈሱበት ፡ ጥቂት ፡ እንዳያስገኝ ፡ ኮረብታም ፡ ሲዘንም ፡ ውሎ፡ ሲዘንም ፡ ቢያድር ፡ ጥርኝ ፡ ውኃ ፡ እንዳይቋጥር ፡ ምስጢር፡ የማይቋጥሩ፡ ናቸው ፡

ወትዕግልት ፡ ምግባሮሙ ፡

ሥራቸውም ፡ ቅሚያ ፡ ነው ፡

ወየጎድጉ ፡ መርገመ ፡ ለውሉዶሙ ።

ለልጆቻቸው ፡ መርገምን ፡ ይተዋሉ ፡ አለ፡ ርጉማን ፡ የርጉማን ፡ ልጆች ፡ ያሰኝዋቸዋል ፡ ሐሰትን ፡ ጥፋትን ፡ ክፉ ፡ ትምህርትን ። አንድም ፡ መርገመ ፡ ጌባልን ። አንድም ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ርጉማን ፡ መባልን ፡ ይተዋሉ ፡ (ያመጣሉ) ።

፲፭ ፤ ወስሕተዋ ፡ ለፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡

ሕገ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልን ፡ ትተው ፡

ወተለውዋ ፡ ለፍኖተ ፡ በለዓም ፡ ወልደ ፡ ባዖር ፡

የባሶር ፡ ልጅ፡ የበለዓምን ፡ ግብር ፡ የያዙ፡

ዘአፍቀራ ፡ ለዐስበ ፡ ዐመፃ ።

የዐመጽን ፡ ዋጋ ፡ የወደዳት ። ሐተታ ፡ ሊባሶር ፡ ቢቀጥሉ ፡ መርገሙ ፡ የዘር ፡ ነው፡ ለበለዓም ፡ ቢቀጥሉ ፡ የተመቸ ፡ በአሪት ፡ ቢያር ፡ ይላል ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ስም ፡ አለው ። አንድም ፡ አንዱ ፡ ያባቱ፡ አንዱ ፡ ያያቱ ፡ ዘኑል ፡ ፳፪ ፡ ፯ ። ራእ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፲፮ ፤ ወተዛለፎ ፡ ለበለዓም ፡ በኃጢአቱ ፡ ዘኢይነብብ ፡ አድግ ፡ በቃለ ፡ እንስሳ ፡ እመሕያው ፡ ተናገረ ፡

በለዓምንስ ፡ ተናግሮ ፡ የማያውቅ ፡ አህያ፡ በቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ተናግሮ ፡ ዘለፈው ፡

ወከልኦ ፡ ለነቢይ ፡ እበደ፡

ስንፍናውንም ፡ አራቀለት ፡ አለ ፡ ደንግጦ ፡ ልመዶስ ፡ አለ ፡ እሊህ ፡ ግን ፡ (እሱ፡ ኢይደነግጹ) ፡ ጌትነቱን ፡ ሲነቅፉ ፡ የማይደነግጹ ፡ ናቸው ። አንድም ፡ በለዓምን፡ ዘለፈው ፡ ስንፍናውም ፡ አህያው ፡ የተናገረውን ፡ ከማወቅ ፡ ከለከለው ። አንድም መልአኩ ፡ የተናገረውን ፡ ኪያሁ ፡ ተዐቀብ ፡ ለነቢብ ፡ ያለውን ፡ ከማወቅ ፡ ከለከለው ፤ እሊህንም ፡ ጌትነቱን ፡ መንቀፍ ፡ እንዳይገባ ፡ ከማወቅ፡ ስንፍናቸው ፡ ከለከላቸው።አንድም፡በለዓምንስ፡ ቁሞ፡ ረግሞ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቢያጠፉ፡ የማይወድ፡ እግዚአብሔር፡ ተቀ
ምጦ ፡ ረግሞ ፡ ቢያጠፉ ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡
ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ እንዳይወድ ፡ ከማ
ወቅ ፡ ስንፍናው ፡ ከለከለው ፡ እሊህንም ፡
ራሳቸው ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ቢጎዱ ፡
የማይወድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብነት ፡
ሆነው ፡ ሌላውን ፡ ቢያስጎዱ ፡ እንዳይ
ወድ ፡ ከማወቅ ፡ ስንፍናቸው ፡ ከለከላ
ቸው ። (ታሪክ) ፡ እስራኤል ፡ በግብፅ ፡
ዘጠኝ ፡ መቅሠፍት ፡ አሥረኛ ፡ ሞተ ፡
በኵር ፡ አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ስጥመት ፡ አድ
ርገው ፡ ወጥተው ፡ በገዳም ፡ ሲዎገን ፡
አግን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ከባላቅ ፡ ወል
ደ ፡ ዖፎር ፡ አገር ፡ ደረሱ ፡ ይህ ፡ በለዓም ፡
ሀብተ ፡ መርገም ፡ የተሰጠው ፡ ነው ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ መጥቶ ፡ በሀገሬ ፡ ሰፍ
ሯልና ፡ መጥተህ ፡ ረግመህ ፡ አጥፋልኝ ፡
ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በዕንቁ ፡ እሠራልሃ
ለሁ ፡ ብሎ ፡ ገንዘብ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡
አስይዞ ፡ ላከበት ፡ ሂደው ፡ ነገሩት ፡ እስኪ
ቆዩ ፡ አምላኬን ፡ ልጠይቅ ፡ ብሎ ፡ ቢጠ
ይቅ ፡ አትሂድ ፡ አለው ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡
አትሂድ ፡ አለኝ ፡ አላቸው ፡ ሂደው ፡ ነገ
ሩት ፡ ሰዎቹ ፡ ተርታ ፡ ቢሆኑበት ፡ ገንዘ
ቡም ፡ ቢያንሰው ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ለደጋግ ፡
ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አስይዞ ፡ ሰደደለት ፡
አሁንም ፡ ቆዩ ፡ አምላኬን ፡ ልጠይቅ ፡
ብሎ ፡ ገባ ፡ ቢጠይቅ ፡ መሂዱን ፡ ሂድ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ አትራገም ፡ እግዚአብሔር ፡
የገለጸልህን ፡ ተናገር ፡ አለው ፡ መላላሽ ፡
ነውላ ፡ ከሂድሁስ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ፡
ብሎ ፡ ወረሐነ ፡ አድጎ ፡ ይላል ፡ አህያ
ውን ፡ ጭኖ ፡ ሲሄድ ፡ መልአክ ፡ ሰይፉን ፡
መዘ ፡ ለአህያይቱ ፡ ታያት ፡ ቆመች ፡ ይመ
ታት ፡ ገሥመረ ፡ እልፍ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፡
ይመታት ፡ ገሥመረ ፡ እልፍ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፡
ይመታት ፡ ገሥመረ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ቆመ
ላት ፡ እልፍ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፡ ይመታት ፡
ዝመረ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ከማያሰኝ ፡ ቅጥ
ርና ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ አጣብቃ ፡ ወመ
ለጠቶ ፡ እገሪሁ ፡ ይላል ፡ እግሩን ፡ ላጠ
ችው ፡ ይመታት ፡ ገሥመር ፡ ለምን ፡ ትመ
ታኛለህ ፡ አለችው ፡ ሰይፍ ፡ ባገኝ ፡ በመ
ታሁሽ ፡ ጦር ፡ ቢኖረኝ ፡ በወጋሁሽ ፡
ነበር ፡ አሮጌ ፡ ነቢይ ፡ አገኘሁ ፡ ብለሽ ፡
ብያ ፡ እንዲህ ፡ ትጫወችብኝ ፡ አለሽ ፡
አላት ፡ እኔማ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ገሥሬ ፡ ሜዳ
ውን ፡ ውጭ ፡ ዐቀበቱን ፡ ሩጭ ፡ ብትለኝ ፡
እምቢ ፡ ብዬህ ፡ አውቃለሁ ፡ እሽ ፡ በጀ ፡
የምልህ ፡ አህያህ ፡ አይደለሁምን ፡ ግሩ
ም ፡ መልአክ ፡ ከፊቱ ፡ ቁሞ ፡ ቢታየኝ ፡
ነው ፡ እንጅ ፡ አለችው ፡ ወዲያው ፡ ሰሱ ፡
ተገለጸለት ፡ ደንግጦ ፡ ወርዶ ፡ አንተ ፡
እንደ ፡ ተቃወምኸኝ ፡ ባላውቅ ፡ ነው ፡
አሁንም ፡ ልመለስ ፡ አለው ፡ መሂዱን ፡
ሂድ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘወደየ ፡ እግዚአብሔር ፡
ውስተ ፡ ልብከ ፡ ኪያሁ ፡ ተዐቀብ ፡ ለነ
ቢብ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለ
ጸልህን ፡ ተናገር ፡ እንጅ ፡ አትራገም ፡
አለው ፡ ሂድ ፡ ሂደው ፡ መጣ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡
ደስ ፡ ብሎት ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበለው ፡ ስለ ፡
መሳህ ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፡ እግዚአብሔር ፡
የገለጸልኝን ፡ እናገራለሁ ፡ እንጅ ፡ አልራ
ገምም ፡ አለው ፡ እንኳን ፡ መጣህ ፡ እን
ጅ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ሰባት ፡ ፍየል ፡
ሰባት ፡ በግ ፡ ሰባት ፡ ላም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡
ተራራ ፡ ወጣ ፡ ያን ፡ ሰውዮ ፡ አልፍ ፡ ብሎ ፡
ተቀመጠ ፡ እሱም ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ራቁ
ቱን ፡ ሆኖ ፡ ያሚርት ፡ ገሥመረ ፡ ወዲያ ፡
ወዲህ ፡ እያለ ፡ ምንተ ፡ እረግም ፡ ዘእግዚ
አብሔር ፡ ኢረገመ ፡ ወምንተ ፡ እጼእል ፡
ዘእግዚአብሔር ፡ ኢጸአለ ፡ አለ ፡ ርግምል

ኝ ፡ ብልህ ፡ ትመርቃለህ ፡ አለው ፡ ነግሬ
ህ ፡ አለሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡
እናገራለሁ ፡ አለው ፡ ከዚህ ፡ ሰፈሩ ፡ ቢታየው ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ ከነገደ ፡ ይሁዳ ፡ በቀር ፡ ሌ
ላው ፡ ከማይታይበት ፡ ቦታ ፡ ወስዶ ፡ ሰ
ባት ፡ ላም ፡ ሰባት ፡ በግ ፡ ሰባት ፡ ፍየል ፡
ሰውቶ ፡ በል ፡ ርገምልኝ ፡ አለው ፡ እሱ
ም ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እ
ያለ ፡ ያሚርት ፡ ገሥመረ ፡ ሚ ፡ ይሜኒ ፡
ተዓይኒከ ፡ እስራኤል ፡ ወእፎ ፡ አብያቲከ ፡
ይሁዳ ፡ አ ለ ፡ ከዚህም ፡ ቢታየው ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ ሁሉም ፡ ከማይታይበት ፡ ወስዶ ፡
ርገምልኝ ። አለው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አይ
ሠዋም ፡ ይሉታል ፡ እምአርእስተ ፡ አድ
ባር ፡ እጼውያ ፡ ወእምአውግር ፡ እሌብዎ ፡
ለእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ዘባሕቲቱ ፡ የጎ
ድር ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ ብሎ ፡ በደኅኖው ፡ ኮኮብ ፡ ይሠርቅ ፡
እምያዕቆብ ፡ ወየአትት ፡ ኃጢአተ ፡ እም
እስራኤል ፡ አለ ፡ እርገምልኝ ፡ ብልህ ፡
እነሆ ፡ ስትመርቅ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛህ ፡
ነው ፡ ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በዕንቁ ፡ እሠ
ራልሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበረ ፡ ላንተ ፡ ቀረብህ ፡
እንጅ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ አለው ፡ ከብ
ተ ፡ ነቢ ፡ እንዲሉ ፡ ምን ፡ ጊዜስ ፡ አንተ ፡
የምትሻው ፡ የእስራኤልን ፡ ጥፋት ፡ አይ
ደለምን ፡ አለው ፡ አዎን ፡ አለው ፡ ቁሞ ፡
ረግሞ ፡ ማጥፋት ፡ ባይቻለኝ ፡ ተቀምጬ ፡
መክሬ ፡ እንዲጠፉ ፡ አላደርግምን ፡ አለው ፡
ይጥፉልኝ ፡ እንጅ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ አለው ፡
አዋልደ ፡ ሞዓብን ፡ መልካሙን ፡ ቆንጆ ፡
እየመረጥህ ፡ ጣዖቱን ፡ ኢያሳዘልኽ ፡ መ
ሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ እያስያዝህ ፡ ስደዳ
ቸው ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ በመና ፡ የተና
ደደ ፡ እስራኤል ፡ አይችልም ፡ ባይዋቸው ፡
ጊዜ ፡ ይሻሙባቸዋል ፡ ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡
መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ ብሉ ፡ ይበሳጫሉ ፡
ለጣዖት ፡ ይሰግዳሉ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖ
ቱን ፡ ይበላሉ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ለአምል
ኩቱ ፡ ቀናኢ ፡ ነውና ፡ ቀንቶ ፡ ያጠፋልሃል ፡
አለው ፡ እንዳለው ፡ አዋልደ ፡ ሞዓብን ፡
መልካካሙን ፡ ቆንጆ ፡ እየመረጠ ፡ ጣዖ
ቱን ፡ እያሳዘለ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡
እያስያዘ ፡ ሰደዳቸው ፡ ከሩቅ ፡ ባይዋቸው ፡
ጊዜ ፡ ተሻሙባቸው ፡ ለጣዖት ፡ ስገዱ ፡
መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ ብሉ ፡ አሏቸው ፡
ለጣዖት ። ስገዱ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡
በሉ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቸነፈር ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ፈጅቷቸዋል ፡ ሁለት ፡ ዕልፍ ፡ ከ
አራት ፡ ሺሕ ፡ አልቀዋል ፡ የእስራኤል ፡
የቤት ፡ አለቃ ፡ ዘምሪ ፡ ይባላል ፡ የአሕ
ዛብ ፡ የቤት ፡ አለቃ ፡ ልጅ ፡ ክስቢ ፡ ትባ
ላለች ፡ ተያይዘው ፡ በስተከበሮ ፡ ቤት ፡
በኩል ፡ ሲያልፉ ፡ ፊንሐስ ፡ አውታረ ፡
ደብተራ ፡ አሪቱ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ሰምቶ ፡
ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሥለት ፡ የገባ ፡
ዘገር ፡ ነበረ ፡ አንሥቶ ፡ ቢወረውረው ፡
ወረገዛ ፡ ማዕከለ ፡ ኅፍረታ ፡ ይላል ፡ ሥራ
ቸውን ፡ በሚሠሩበት ፡ በኩል ፡ አጸምሯ
ቸዋል ። ጌታም ፡ አ ፡ ፊንሐስ ፡ ወልደ ፡ አላ
ዛር ፡ ወልደ ፡ አሮን ፡ አስተንፈስካ ፡ ለል
ብየ ፡ ልቡናዩን ፡ ደስ ፡ አሰኘሃት ፡ ብሎ
ታል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ መዋዕል ፡ ክህነት ፡ ተጨምሮለታ
ልና ፡ ዘአፍቀራ ፡ ለዐስበ ፡ ዐመፃ ፡ አለ ፡
ዘልኑ ። ፳፪ ። ፳፭ ።

፲፯ ፤ እሉ ፡ እሙአቱ ፡ ወዘቅት ፡ ንጽፍት ፡
ደረቅ ፡ ወንዞች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡
ወጊሜ ፡ ዘነፋስ ፡ ይዘርም ፡
ነፋስ ፡ የሚበትነው ፡ ደመና ፡ እሊህ ፡
ናቸው ። ሐተታ ፡ ወንዝ ፡ ሲባል ፡ ውኃ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዳያስገኝ ፡ ደመና ፡ ሲባል ፡ ዝናም ፡ እንዳያዘንም ፡ (እንዳያስገኝ) ፡ እሊህም ፡ መምህራን ፡ ሲባሉ ፡ ምሥጢር ፡ አያስገ ኙምና ። አንድም ፡ ነጋድያን ፡ ከዕሩቅ ፡ ዛፉ ፡ ረዝሞ ፡ ቅጠሉ ፡ ለምልሞ ፡ አይ ተው ፡ ከዚያ ፡ ወንዝ ፡ ደርሰን ፡ ኩበታች ነን ፡ አራግፈን ፡ ዳቧችንን ፡ ጐርሰን ፡ ውኃችነን ፡ ጠጥተን ፡ ከጥላው ፡ አርፈን ፡ እንሄዳለን ፡ ብለው ፡ ይሄዳሉ ፡ ሂደው ፡ ሲያጠበት ፡ ተስፋ ፡ ይቈርጣሉ ፡ ደመናም ፡ በዞረ ፡ ጊዜ ፡ ገበሬ ፡ እርሻውን ፡ በቅብ ቅብ ፡ አድርጎ ፡ ዘሩን ፡ በዕንቅብ ፡ ይዞ ፡ ይጠብቃል ፡ ነፋስ ፡ መጥቶ ፡ በበተነው ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ ይቈርጣል ፡ እሊህም ፡ አም መው ፡ ጠምቀውው ፡ መነሳንሳቸውን ፡ ይዘው ፡ ሰናፊላቸውን ፡ አንሰርተው ፡ ልብ ሳቸውን ፡ አንጽተው ፡ ባይዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ያልተማሩት ፡ እንማራለን ፡ የተማሩት ፡ ምሥጢር ፡ እንረዳለን ፡ ብለው ፡ ይሄዳሉ ፡ ደርሰው ፡ ምሥጢር ፡ ሲያጠባቸው ፡ ተስፋ ፡ ይቈርጣሉና ። አንድም ፡ (ዐበቅ ት ፡ ንጽፍት) ፡ ተርታ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ምላሽ ፡ የሚያሳጣቸው ፡ (ወጊሜ ፡ ዘነ ፋስ) ፡ ጥቂት ፡ ጎይለ ፡ ቃል ፡ የሚረታ ቸው ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡

እለ ፡ ለዶይነ ፡ ጽልመት ፡ የዐቅብሞሙ ።

ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ ለማያልፍ ፡ ጽኑ ፡ ፍኖ ፡ የሚጠብቋቸው ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ዐበይተ ፡ ጌጋይ ፡ ነበቡ ፡

የኃጣውኡ ፡ ደጋጉን ። አንድም ፡ ዓበይተ ፡ ጌጋየ ፡ ደጋጉን ፡ ኃጣውእ ፡ ተናግረዋ ልና ፡ አለ ፡ ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ ማለት ፡ ነው ። አንድም ፡ ዓበይተ ፡ ጌጋይ ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ የማይገባን ፡ ነገር ፡ ተናግረዋልና ፡ ወያደነግው ፡ በእንተ ፡ ፍትወተ ፡ ዝሙቶሙ ፡ ዘሥ ጋሆሙ ፡

በሥጋቸው ፡ የሚሠራ ፡ ዝሙትን ፡ ስለ ፡ መውደድ ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ያሸብራሉ ።

ሰብእ ፡ እለ ፡ ጎዳጠ ፡ አምሰጡ ፡ ወገብኡ ፡ ውስተ ፡ ጌጋይ ።

ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከአሪት ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ የተመለሱ ። ሐተታ ፡ ጌጋይ ፡ አላት ፡ ትለፍ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ቢይዝዋት ፡ ፍዳን ፡ የምታመጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፲፪ ፤ እለ ፡ ሕገ ፡ ግዕዛን ፡ ተምህሩ ፡

ሕገ ፡ ግዕዛን ፡ ወንጌልን ፡ ተምረው ፡

ወለሊሆሙኒ ፡ ቅኑያን ፡ ለሕርትምና ፡

ጥፋት ፡ ሊሆንባቸው ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣባ ቸው ፡ ለአሪት ፡ የተገዙ ፡

እስመ ፡ ዙሉ ፡ ለዘተአዘዘ ፡ ውእቱ ፡ ይትቀነይ ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለታዘዘለት ፡ ይገዛልና ፤ ቅኑ ያን ፡ ላለው ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፬ ።

፲፫ ፤ እስመ ፡ ለእመ ፡ ጐዩ ፡ እምኃጢአቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ በእእምሮቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስን ፡ በማወቅ ። አንድም ፡ በማወቅ ፡ ላይ ። አንድም ፡ ከማወቅ ፡ ጋራ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ኃጢአት ፡ ከአሪት ፡ ተለይተው ፡ ነበረና ፡ እለ ፡ ጎዳጠ ፡ አምሰጡ ፡ ላለው ፡

ወገብኡ ፡ ዳግመ ፡

ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ተመልሰዋልና ፡ ቅኑያን ፡ ላለው ፡

ወተጸፍሩ ፡ ወተቀንዩ ፡ ሎቱ ፡

በአሪት ፡ ጸንተዋልና ፡ ገብዑ ፡ ውስተ ፡ ጌጋይ ፡ ላለው ። ሐተታ ፡ ተጸፍሩ ፡ ተቀ ንዩ ፡ ማለቱ ፡ የተፈተለ ፡ ከሁለት ፡ የተ ታታ ፡ ከሦስት ፡ እንዲሉ ፡ ከተፈተለ ፡

የተታታ ፡ እንዲጸና ፡ ተመልሰው ፡ በአ ሪት ፡ ጸንተዋልና ፡ ተጸፍሩ ፡ አለ ፡

ወይክውኖሙ ፡ ደኃሪ ፡ ጌጋዮሙ ፡ እምነ ፡ ቀዲሙ ፡ ዘየአክዮሙ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ከቀደመ ፡ በደላቸው ፡ የኋ ላው ፡ በደላቸው ፡ የጸና ፡ የከፋ ፡ ይሆናል ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ።

፳፩ ፤ እምኀየሶሙ ፡ ሶበ ፡ ኢያእመርዋ ፡ ለፍናተ ፡ ጽድቅ ፡ እምያእምርዋ ፡

ጥንቱን ፡ ሕገ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልን ፡ ኪያው ቋት ፡ ባያውቋት ፡ በተሻላቸው ፡ ነበረና ፡

ወይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ እምእንተ ፡ ተውህበት ፡ ሎሙ ፡ ትእዛዝ ፡ ቅድስት ።

ነገር ፡ ግን ፡ አውቀዋት ፡ ከተሠራችላቸው ፡ ከክብርት ፡ ሕግ ፡ ከወንጌል ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ ኪመለሱ ። አንድም ፡ እም ዘተወፈዩ ፡ ትእዛዘ ፡ ቅድስተ ፡ ይላል ፡ ክ ብርት ፡ ወንጌልን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ት ትሐነፂ ፡ እምዘነሠቱኪ ፡ ወእምዘረወዩ ፡ አግማሊሁ ፡ ነሥአ ፡ ኢያቡር ፡ አዕኑገ ፡ ዘ ወርቅ ፡ እንዲል ፡ ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፶፯ ።

፳፪ ፤ ወበጽሐቶሙ ፡ አምሳልኡ ፡ እንተ ፡ መሰሉ ፡ በጽድቅ ፡

በጽሐቶሙ ፡ በጽድቅ ፡ እንተ ፡ መሰሉ ፡ በጽድቅ ፡ (ብለህ ፡ ግጠም) ፡

እንተ ፡ ይቤ ፡ ክልብ ፡ ገብአ ፡ ዲበ ፡ ቅያዩ ፡ ወሐራ ውያኒ ፡ ተሐሚባ ፡ ገብአት ፡ ዲበ ፡ ጸብር ።

ሰሎሞን ፡ ክልብ ፡ ገብአ ፡ ዲበ ፡ ቅያው ፡ ሚራክም ፡ ወሐራውያኒ ፡ ተሐሚባ ፡ ገብአት ፡ ዲበ ፡ ጸብር ፡ ብለው ፡ በዕውነት ፡ መስ ለው ፡ የተናገሩት ፡ ነገር ፡ በዕውነት ፡ ደረ ሰባቸው ። ሐተታ ፡ የሰሎሞንስ ፡ ይሁን ፡ ከሲራክ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ወዲት ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ተናግሮት ፡ ሳይጸፍ ፡ የቀረ ፡ ነው ፡ ተነግሮ ፡ ሳይጸፍ ፡ የቀረውንም ፡ ማም ጣት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ተዐቀቡ ፡ በመዋ ዕለ ፡ አዕራር ፡ ያለውን ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ኢያብ ፡ እንዳሉ ፡ ሐዋርያት ። አንድም ፡ እንተ ፡ መሰለ ፡ በጽድቅ ፡ ሰሎሞን ፡ ወዘ ጽሉአ ፡ ይከውን ፡ ያለውን ፡ እንዲህ ፡ ለውጦ ፡ አነበበው ። አንድም ፡ ጌታ ፡ ማቴ ዎስ ፡ በዕውነት ፡ መስለው ፡ የተናገሩት ፡ ነገር ፡ በዕውነት ፡ ደረሰባቸው ፡ ኢተሀቡ ፡ ቅድሳተ ፡ ለከለባት ፡ ወኢትደዩ ፡ ባሕር የክሙ ፡ ቅድመ ፡ አሕርው ፡ ብለው ። አን ድም ፡ እንተ ፡ መሰልነ ፡ ሰሎሞን ፡ ከልብ ፡ ገብአ ፡ ዲበ ፡ ቅያኡ ፡ እኔ ፡ ወሐራውያኒ ፡ ተሐሚባ ፡ ገብአት ፡ ዲበ ፡ ጸብር ፡ ብለን ፡ በዕውነት ፡ መስለን ፡ የተናገርነው ፡ ነገር ፡ በዕውነት ፡ ደረሰባቸው ፡ ጸብር ፡ ባለው ፡ ሚለሃ ፡ አንቃሶ ፡ የሚል ፡ አብነት ፡ ይገ ኛል ። ሐተታ ፡ የዕሪያ ፡ ገላው ፡ ትኩስ ፡ ቁርበቱ ፡ ስስ ፡ ነው ፡ ዋዕየ ፡ ፀሓይ ፡ ሲሰ ማው ፡ ሂዶ ፡ ከጭቃ ፡ ይንከባለላል ፡ ከው ኃ ፡ ይታጠባል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይኖራል ፡ እሊህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሉ ፡ ይኖራሉና ፡ ምሳ ፡ ፳፮ ፡ ፲፩ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ክፍል ፡ ፫ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ አኀውየ ፡ ዳግሚ ትየ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለኩሙ ፡ መጽሐፈ ፡

ወንድሞቼ ፡ ሁለተኛ ፡ የጻፍሁላችሁ ፡ ክታብ ፡ ይህች ፡ ናት ። አንድም ፡ ዛት ፡ መጽሐፈ ፡ ሁለተኛ ፡ ይህችን ፡ ክታብ ፡ ጸፍሁላችሁ ። ሐተታ ፡ ፈረንጅ ፡ ይህን ፡ ይዞ ፡ የጴጥሮስ ፡ ክታብ ፡ ሦስት ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ሁለት ፡ ነው ፡ ሁለተኛነቱም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለቀዳሚት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለዳግሚት ፡ አይደለም ፡

ከመ ፡ እንሥእከሙ ፡ በዘክሮ ።

ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ትንግሌ ፡ ሙታን ፡ ኅልፈት ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እንዳሲ ፡ በማሳሰብ ፡ አነቃቃችሁ ፡ ዘንድ ፡

ወትዕቀብዋ ፡ በልብከሙ ፡ ለጽድቅ ፡

ሃይማኖትን ፡ በልቡናችሁ ፡ ሣጥንነት ፡ ትጠብቋት ፡ ዘንድ ፡ (ትይዟት ፡ ዘንድ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።

፪ ፤ ወከመ ፡ ትዘክሩ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ቀደምት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘይቤሉ ።

ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ እንዳለ ፡ ቀደምት ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩትን ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ ሙሴ ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ዳዊትም ፡ አንተ ፡ እግዚእ ፡ አቀደምከ ፡ ሣርዮታ ፡ ለምድር ፡ ወግብረ ፡ እደዊከ ፡ እማንቱ ፡ ሰማያት ፡ ኢሳይያስ ፡ እዴየ ፡ ሣረረታ ፡ ለምድር ፡ ወየማንየ ፡ አጽንዐቶ ፡ ለሰማይ ፡ ሰማይኒ ፡ መንበርየ ፡ ወምድርኒ ፡ መከየዳ ፡ እገርየ ፡ ዓየኑ ፡ ቤተ ፡ ተሐንጹ ፡ ሊተ ፡ ለመካነ ፡ ምዕራፍየ ፡ ዕዝራም ፡ አኮኑ ፡ አንተ ፡ ትቤ ፡ አመ ፡ ፈጠርክሃ ፡ ለምድር ፡ ከመ ፡ ታውጽኦ ፡ ለአዳም ፡ በሥጋ ፡ መዋቲ ፡ ብለው ፡

ወትእዛዘ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኀኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘአዘዘ ፡ ለነ ፡ ለሐዋርያት ።

ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ እንዳለ ፡ ለኛ ፡ ለሐዋርያት ፡ የነገረንን ፡ ነገር ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ ወባሕቱ ፡ ርቱዕ ፡ ሊተ ፡ እገብር ፡ ግብሮ ፡ ለዘፈነወኒ ፡ እንዘ ፡ መዓልት ፡ ውእቱ ፡ አቡየኒ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ይገብር ፡ ወአነኒ ፡ እገብር ፡ ብሎ ። አንድም ፡ ትንሣኤ ፡ እንዳለ ፡ ቀደምት ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩትን ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ አዩብ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ እሄሉ ፡ በዝንቱ ፡ ሥጋየ ፡ ዘቍሱሕ ፡ በደም ፡ እስከ ፡ አንተ ፡ ትሔድሶ ፡ ዕዝራም ፡ ወይነቅህ ፡ ዓለም ፡ ዘመዋቲ ፡ ዘአልቦ ፡ አመ ፡ ነቅሀ ፡ ኢሳይያስም ፡ ሙታን ፡ ይትነሥኡ ፡ ወየሐይዉ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ዳዊትም ፡ ትፈኑ ፡ መንፈስከ ፡ ወይትፈጠሩ ፡ ብለው ፡ ጌታም ፡ ትንግሌ ፡ ሙታን ፡ እንዳለ ፡ ለኛ ፡ እለሰ ፡ እኩየ ፡ ገብሩ ፡ ይወፅኡ ፡ ውስተ ፡ ትንግሌ ፡ ዘለደይን ፡ ወእለሰ ፡ ሠናየ ፡ ገብሩ ፡ ይወፅኡ ፡ ውስተ ፡ ትንግሌ ፡ ዘለሕይወት ፡ ብሎ ፡ የነገረንን ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እንዳለ ፡ ቀደምት ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩትን ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊት ፡ እማንቱሰ ፡ ይትሐጕሳ ፡ ዕዝራም ፡ ወይሴስል ፡ ዓለም ፡ ዘመዋቲ ፡ ወይኅብእ ፡ ጎበ ፡ ዘትኪት ፡ ምንባሪሁ ፡ በጎበ ፡ ያረምም ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕል ፡ ብለው ፡ ጌታም ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ የኅልፍ ፡ ወቃልየሰ ፡ ኢየኀልፍ ፡ ብሎ ፡ ለኛ ፡ ለሐዋርያት ፡ የነገረንን ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ላለው ፡ ነው ።

፫ ፤ ወዘንተኒ ፡ ቅድሙ ፡ አእምሮ ።

ይህንንም ፡ አስቀድማችሁ ፡ ዕወቁ ፡

ከመ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይምጽኡ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ መስተአብዳን ፡ ለአስተአብዶ ፡

ለራሳቸው ፡ ሰንፈው ፡ ሰውን ፡ የሚያሰንፉ ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እንዲነሡ ፡ ዕወቁ ፡

እለ ፡ የሐውሩ ፡ በፍትወተ ፡ ልቦሙ ።

ልቡናቸው ፡ በወደደው ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፬ ፤ ወይብሉ ፡ አይቴ ፡ ውእቱ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ሀለዎ ፡ ይምጻእ ፡

ወአመ ፡ ይመጽእ ፡ ብሏል ፡ ትላላችሁ ፡ ከመጣማ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይመጣልን ፡ አስቀድሞ ፡ ፈታውራሪው ፡ ደጀዝማቹ ፡ እያለ ፡ አይ ደለምን ፡ እንደዚህስ ፡ ሁሉ ፡ ከመላእክት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ አይመጡምን ፡ የሚሉ ፡ (እያሉ) ፡ ለራሳቸው ፡ ሰንፈው ፡ ሰውን ፡ የሚያሰንፉ ፡ ሰዎች ፡ እንዲነሡ ፡ ዕወቁ ፡

ወአመሰ ፡ አበዊነ ፡ ቀደምት ፡ ሞቱ ።

ትንግሌ ፡ ሙታን ፡ አለ ፡ ትላላችሁ ፡ አመሰ ። ትንግሌ ፡ ሙታንማ ፡ ካለ ፡ የቀደሙ ፡ አባቶቻችን ፡ እነሆ ፡ ሙተዋል ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ አይነሡም ፡ ገቢያ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይመላልን ፡ ጦር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበሰባልን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያለ ፡ አይደለምን ፡

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘሀለወ ፡ በከመ ፡ ሀሎ ፡ እም ፍጥረተ ፡ ዓለም ።

ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ አለ ፡ ትላላችሁ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ የተፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድርማ ፡ ካለ ፡ ከሰማየ ፡ ተንዶ ፡ ከምድሩ ፡ ተቆርሶ ፡ አይወድቅለትምን ፡ ግን ብ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይናዳልን ፡ አንድ ፡ ክረምት ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ አንድ ፡ ክረምት ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ እያለ ፡ አይደለምን ፡ መከር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳልን ፡ አንድ ፡ ወራት ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ አንድ ፡ ወራት ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ እያለ ፡ አይደለምን ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ። ሕዝ ፡ ፲፪ ፡ ፳፪ ። ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፮ ።

፭ ፤ ወኢያእመርዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ከመ ፡ ሰማያትኒ ፡ ተፈጥራ ፡ እምትካት ፡

ሰማያት ፡ ጥንቱን ፡ ለኅልፈት ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩ ፡ ይህን ፡ አያውቁምና ፡

ወምድርኒ ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ወበማይ ፡ ጸንዐት ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ምድርም ፡ ጥንቱን ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ ለኅልፈት ፡ እንደ ፡ ተፈጠረች ፡ አያውቁምና ፡ ለይኩን ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡ እንጅ ። ሐተታ ፡ ምድር ፡ ምን ፡ ትመስላለች ፡ ቢሉ ፡ ሰውን ፡ ሰው ፡ በአጥንት ፡ በደም ፡ በጅማት ፡ በሥጋ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ምድርም ፡ እንደ ፡ አጥንት ፡ አእባን ፡ እንደ ፡ ጅማት ፡ አሥራው ፡ ዕፅ ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ውኃ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ መሬት ፡ ሁና ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለችና ፡ ማቴ ፡ ፭፬ ፡ ፴፭ ። ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፭፬ ፡ ፪ ።

፮ ፤ ወዓለመ ፡ ትካትኒ ፡ ቦቱ ፡ አጥፍአ ፡ በማየ ፡ ዓይን ።

በቅጥል ፡ ያመጣውን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ አመጣው ፡ የምሥጢር ፡ ቅጥል ፡ የምሥጢር ፡ ባለቤት ፡ ነው ፡ ሰብአ ፡ ትካትንም ፡ በውኃ ፡ አጠፋ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፭ ። ዘፍጥ ፡ ፯ ፡ ፳፩ ።

፯ ፤ ወይእዜኒ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ በውእቱ ፡ ቃል ፡ ዝኑባን ፡ ወዕቁባን ፡ እሙንቱ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ ወድምሳሴ ፡ ኃጥኣን ፡ ሰብእ ፡

እንኪያስ ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ ኃጥኣን ፡ ሰዎች ፡ እስከሚጠፉባት ፡ እስከ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለይኩን ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ለኅልፈት ፡ ደልበዋል ፡ ተጠብቀዋል ፡ ቍ ፡ ፭ ።

፰ ፤ ወዘንተ ፡ ባሕቱ ፡ ኢትርስዑ ፡ አኀዊነ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ይህን ፡ ዕወቁ ፡ አለ ፡ ዳዊት ፡ የተናገረውን ፡ ዕወቁ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ፡ በጎበ ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ።

በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አንዲቱ ፡ ቀን ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሽሕ ፡ ዘመን ፡

ወዐሠርቱ ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡ ከመ ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ።

በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሽሕ ፡ ዘመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ የተናገረውን ፡ ዕወቁ ፡ መዝ ፡ ፺ ፡ ፬ ።

፬ ፤ ኢያጕነዲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ዘነበበ ፡

እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ አያስቀርምና ።

እስመ ፡ ቦ ፡ አለ ፡ ይብሉ ፡ ከመ፡ ይጕነዲ ፡

እንዲቀር ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች፡ ስለ፡ አሉ ፡ (ጥቅ) ፡ ሞተ፡ ወልድየ ፡ ወበእንተ፡ ዝ ፡ ጕንደያ ፡ እንዲል ፡

ወባሕቱ ፡ ይትዔገሥ ፡ በእንቲአሆሙ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ስለሳቸው ፡ የሳቸውን ፡ ነገር ፡ ይታገሣል ። አንድም ፡ ይታገሣል ፡ እንጅ ፡ ኢያጕነዲ ፡ ላለው ፡

እስመ ፡ ኢይፈቅድ ፡ መነሂ፡ ያማስን፡ (መኑሂ ፡ ይማስንም ፡ ይላል) ፡

ማነንም ፡ ማንን ፡ ፈጥኖ ፡ ሊያጠፋ ። አንድም ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ፈጥኖ ፡ ሊጠፋ ፡ አይወድምና ፡

አላ ፡ ይንስሑ ፡ ለዝኩ ፡ ሰብእ ፡ ያርሕብ ።

ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ወራት ፡ አስፍቶ ፡ ዘመን ፡ አጠዝቶ ፡ ይሰጣል ፡ እንጅ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ያማስን ፡ ላለው ፡ እንባ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ፭ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፲ ፤ ወዕለቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግብተ ፡ ትመጽእ፡ ከመ ፡ ሠራቂ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ የሚመጣበት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ሌባ ፡ ባላወቁት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ሰዓት ፡ ድንገት ፡ እንዲመጣ ፡ ባላወቁት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ሰዓት፡ ድንገት ፡ ትደርሰለች ፡

እንተ ፡ ባቲ ፡ ሰማያትኒ ፡ ይትረኀዋ ፡ ወይሰሰላ ፡

ሰማይና ፡ ምድር ፡ የሚያልፉባት ። ሐተታ ፡ ይትረኀዋ ፡ ብሎ ፡ በግሥ ፡ ተናግሮ ታል፡ (ጥቅ)፡ ወአስተጣበቅዋ፡ ዲበ፡ እብነ፡ ከሑሕ ፡ እንዲል ፡ አድማስ ፡ እንደ ፡ መሶብ ፡ እንደ ፡ ወጭት ፡ ጠፈር ፡ እንደ ፡ መሶብ፡ እፍያ፡ እንደ፡ ወስከንቢያ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉና ። አንድም ፡ (ዘእንበለ ፡ ድምፅ ፡ ይላል) ፡ ደመና ፡ ጥላውን ፡ ጥሎ ፡ ሳይ ሰማ ፡ እንዲያልፍ ፡ ሳይሰሙ ። አንድም ፡ ሳይከራከሩ ፡ ያልፋሉ ፡ ጥንቱንስ ፡ ለምን ፡ ፈጠርኽን ፡ ዛሬስ ፡ ለምን ፡ ታሳልፈኖ ለህ ፡ ብለው ፡

ወኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ዘቀዲሙ ፡ በውእየተ ፡ እሳት ፡ ይትመሰው ።

አስቀድሞ ፡ የተፈጠረ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልፋል ፡

ወምድርኒ ።

ምድርም ፡ ታልፋለች ፡

ወኵሉ ፡ ዘላዕሌሃ ፡ ግብር ፡ ይውዲ ።

ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለውም ፡ ሁሉ ፡ ያልፋል ፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ቊ ፡ ፯ ። ማቴ ፡ ፳፬ ። ፳፱ ። ራእ ፡ ፳ ፤ ፲፩ ።

፲፩ ፤ ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ተመሲዎ ፡ ጕጕኤ ፡ ከመ ፡ ተሀልዉ ፡ በምግባር ፡ ቅዱስ ፡ ዘጽድቅ ፡

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ጕጕኤ ፡ ሰምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ፡ ከመ ፡ ተሀልዉ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ። አንድም፡ (ከመ ፡ ተሀልዉ ፡ በምግባር ፡ ቅዱስ)፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ በሚመሰገንባት፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ አስቀድ ማችሁ ፡ ጕጕኤ ፡ ሰምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ።

፲፪ ፤ እንዘ ፡ ትሴፈዉ ፡ ወትጋጕኡ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ሰማያትኒ ፡ ይረስና ፡ ወይትመስዋ ፡ ወኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ይውዲ ፡ ወይትመሰው ፡

ሰማያት ፡ የሚያልፉባት ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ የሚያልፍባት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመጣባት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአትን ፡ ተስፋ ፡ አድርጋችሁ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ።

፲፫ ፤ ሐዳሳተ ፡ ሰማያተ ፡ ወሐዳስ ፡ ምድረ ፡ ንሴፎ፡

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ካለፈ ፡ እኛ ፡ እንደምን ፡ ሆነን ፡ እንኑራ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሐዲሱን ፡ ሰማይ ፡ ሐዲሱን ፡ ምድር ፡ ወርሰን ፡ እንድንኖር ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፤

ዘውስቴቶን ፡ የኀድር ፡ ጽድቅ ፡

ባለማለፍ ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ (ጥቅ) ፡ ወጕንድዮታ ፡ ያጤይቅ ፡ ጽድቀ ፡ ዚአሃ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ (ዘውስቴቶን ፡ የኀድር ፡ ጽድቅ) ፡ ጌታ ፡ አድሮባት ፡ የሚኖር ። ሐተታ ፡ ጽድቅ ፡ አለው ፡ በማብሩ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ምድር ፡ አላት ፡ ምድር ፡ አልፋ ፡ በምድር ፡ ቦታ ፡ የምትተካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በምድር፡ በሠራት፡ ሥራ ፡ የምትወረስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምድራውያን ፡ ጻድቃን ፡ የሚወርሷት፡ ስለ ፡ ሆነ፡ በምድር ፡ ተድላ ፡ ሥጋ ፡ ይፈጸማል ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይም ፡ ተድላ ፡ ነፍስ ፡ ይፈጸማልና ፡ ሰማይ ፡ አላት ፤ ሰማይ ፡ አልፋ ፡ እሷ ፡ የምትተካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰማያውያን ፡ መላእክት ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሐዳስ ፡ አላት ፤ በተሐድሶ ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ፡ ታድሰው ፡ ተነሥተው ፡ የሚወርሷት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከመታየት ፡ እንግዳ ፡ ስለ ፡ ሆነች ።

፲፬ ፤ ወይእዜኒ ፡ አኀውየ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትሴፈዉ፡ ጕጕኤ ፡

እንደዚህም ፡ ከሆነ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ይህን ፡ ተስፋ ፡ አድርጋችሁ ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ ቸኩሉ ፡

ይርከብክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ርስሐት ፡ ወዘእንበለ ፡ ጌጋይ ፡

ኃጢአት ፡ በደል ፡ የሌለባችሁ ፡ ሁናችሁ፡ ያገኛችሁ ፡ ዘንድ ፡

እንዘ ፡ ትሰነአዉ ።

በፍቅር ፡ አንድ ፡ ሁናችሁ ።

፲፭ ፤ ወትዕግሥቱሰ ፡ ለእግዚእነ ፡ የሀብክሙ ፡ መድኀኒተ ፡

ወባሕቱ ፡ ይትኤገሥ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነዋ ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጌታችንስ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ንስሓን ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ፡ ነው ። ሐተታ ፡ መድኀኒት ፡ አለው ፡ ንስሓን ፡ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ የሚገኝበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

በከመ ፡ እጉነ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘናፈቅር ፡ ጸሐፈ ፡ ለክሙ፤

የምንወደው ፡ ወንድማችን ፡ ጳውሎስ ፡ የንስሓን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ጻፈላችሁ ፡ ኢቀ አምርኑ ፡ ከመ ፡ ምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያክ ፡ ያገርር ፡ ኀበ ፡ ንስሓ ፡ ብሎ፤

በእንተ ፡ ዘወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበበ ።

እግዚአብሔር ፡ ጥበቡን ፡ ስለ ፡ ገለጸለት ፡ ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፲፮ ፤ በከመ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሁሉ ፡ መጻሕፍቲሁ ፡ ዘነበበ ፡ ውስቴቶን ፡ በእንቲአሁ ፡ ለዝንቱ ።

የንስሓን ፡ ነገር ፡ በተናገረባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ እንዳለ ። አንድም ፡ የጌታችንስ ፡ ትዕግሥት ፡ ትንሣኤን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያደርግላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ (ጥቅ)፡

www.ethiopianorthodox.org

ድኂኖ ፡ አድኅኖሙ ፡ አኮ ፡ ዘድኅነ ፡ ባሕቲቱ፡ አላ፡ አድኅነ፡ ካልአነ፡ ወይዴመሙ፡ በእንተ ፡ መንክር ፡ ዳኅናሁ ፡ ወይመጽእ ፡ በመድኀኒት ፡ ጽኑዕ ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንዲል ። የምንወደው ፡ ወንድ ማችን ፡ ጳውሎስ ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ። እስመ ፡ አቅደመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርእየ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ኢይሠለጡ ፡ ዘእንበሌነ ፡ ብሎ፡ (ዋቅ)፡ ቀደ ሙነ ፡ በተጋድሎ ፡ ወኢቀደሙነ ፡ በነሚአ ፡ አክሊል ፡ ወለዝንቱ ፡ ረሰይክዋ ፡ ከመ ፡ ኅል ቀት ፡ እንዲል ። እግዚአብሔር ፡ ጥበቡን ፡ ስለ ፡ ገለጸለት ፡ የዚህን ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታ ንን ፡ ነገር ፡ በተናገረባቸው ፡ በአሥራ ፡ አ ራቱ ፡ ክታብ ፡ ተጽፎ ፡ እንዳለ ፡ ሐተታ ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ነገር ፡ ያልተናገረበ ት ፡ የለምና ፡ በፊልሞና ፡ ስንኳ ፡ ጸጋ ፡ ብሎታል ፡

ወዘሰ ፡ ነበቡ ፡ እሙራን ፡ እሙንቱ ፡ አለ ፡ ይሴብ ውዎ ።

የጳውሎስ ፡ መጻሕፍት ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ። አንድም ፡ ነበበ ፡ ይላል ፡ ጳውሎስ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ አውቀው ፡ የተረ ጐሙ ፡ ሊቃውንት ፡ (እሙራን) ፡ የታ ወቁ፡ ደጋግ፡ ናቸው፤ ሦስቱ ፡ ጎርጎርዮሳት ፡ እለቄርሎስ ፡ እለአትናቴዎስ ፡ እለዮሐ ንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ባስልዮስ ፡ ጌርሎስ ። አንድም ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ኅልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እንዳለ ፡ አውቀው ፡ የተናገሩ ፡ ነቢያት ፡ የታወቁ ፡ ደጋግ ፡ ናቸው ፤ ሙሴ ፡ ኢዮብ ፡ ዳዊት ፡ ኢሳይያስ ፤ ዕዝራ ፡

ወእለሰ ፡ አልቦሙ ፡ ትምህርት ፡ እለ ፡ ኢለበዉ ፡ ይመይጥዎ ፡ ለቃለ ፡ መጽሐፍ ፡

ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የመጽሐፍን ፡ ቃል ፡ ይለውጣሉ ፡

ከመ ፡ ሚጥዎን ፡ ለብዙኃት ፡ መጻሕፍት ፡ ለማዕዘመ ፡

ለራሳቸው ፡ እንደሚሰማማቸው ፡ እንደ ሚመቻቸው ፡ አድርገው ፡ ብዙዎችን ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ለወጡ ፡ ሐተታ ፡ ናሁ ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ያለውን ፡ ለሕ ዝቅያስ ፡ ሰጠው ፡ እንደ ፡ ተረጐሙ ፡ ድን ግል ፡ የተባለች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ፡ ወልድ ፡ የተባልህ ፡ አንተ ፡ ነህ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ነግሦባት ፡ አያውቀምና ፡ ብለው ፡ እብን ፡ ዘመነንዋ ፡ ነደቅት ፡ ያለ ውን ፡ ለዘሩባቤል ፡ ሰጥተው ፡ እንደ ፡ ተረጐሙ ፡ (በቂ ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለጊዜው ፡ ምሳሌ ፡ ነው) ፡

ወያማስኑ ፡

መጻሕፍትን ፡ ይለውጣሉ ። አንድም ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ይለውጣሉ ። አንድም ፡ (ይማስኑ) ፡ ራሳቸው ፡ ይጠፋሉ ።

፲፯ ፤ ወአንትሙሰ ፡ አኀዊነ ፡ አቅድሙ ፡ አእምሮ ፡ እናንተስ ፡ ወንድሞቻችን ፡ አስቀድማ ችሁ ፡ ይህን ፡ ዕወቁ ፡

ወተዐቀቡ ፡ ከመ ፡ ኢትስሐቱ ፡ ዕዘኢይዕቁዕ ፡ ትም ህርት ፡

በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ትምህርት ፡ እንዳትክዱ ፡ ተጠንቀቁ ፡

ከመ ፡ ኢትደቁ ፡ እምን ፡ ምጽናዕክሙ ።

ከዕኑዕ ፡ አንባ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ እንዳት ወጡ ፡ (እንዳትናወጡ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ፡ ማር ፡ ፲፫ ፡ ፭ ፡ ፱ ። ፴፫ ፡

፲፰ ፤ ተባዝኑ ፡ በእግዚእነ ።

ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ።

ወበአኰቴቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኀኒነ ።

መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማመስገን ፡ (በማገልገል ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው) ።

ወለእግዚአብሔር ፡ አብ ።

እግዚአብሔር ፡ አብንም ፡ በማመስገን ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ። ሐተታ ፡ ለልማዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ አስቀድሞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያደርጋል፤ ከዚህ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አስቀ ድሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አደረገ ፡ ለማስተካከል ፡ ዕሪናቸውን ፡ ለመንገር ፡

ዘለሰቱ ፡ ስብሐት ፡

ክብር ፡ ምስጋና ፡ ጌትነት ፡ ግንዘቡ ፡ የሚ ሆን ።

ይእዜኒ ፡

ከዛሬ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡

ወዘልፈኒ ።

ከዕለተ ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡

ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡

ከዕለተ ፡ ምጽአት ፡ በኋላ ፡ ስብሐት ፡ ላለው ፡

አሜን ፡ ወአሜን ።

ይሁን ።

መልእክት ፡ መልእክተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዳግሚት ።

ሁለተኛዪቱ ፡ የጴጥሮስ ፡ ክታብ ፡ ደረ ሰች ፡ ተፈጸመች ።

www.ethiopianorthodox.org